# በ‹‹ቬነስያና ሌሎች›› እና በ‹‹ከሰይጣን ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅና ሌሎች››

# በሚሉ ሁለት መፅሀፎች ውስጥ የሚገኙ ግጥሞች የይዘት ትንተና

በ

ፋሲካ አድማሱ

የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች

ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ሰኔ 2002 ዓ.ም

# በ‹‹ቬነስያና ሌሎች›› እና በ‹‹ከሰይጣን ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅና ሌሎች››

# በሚሉ ሁለት መፅሀፎች ውስጥ የሚገኙ ግጥሞች የይዘት ትንተና


በ

ፉሲካ አድማሱ


የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች

ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ


አማካሪ  መሀሪ ዘመልዐክ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ


ሰኔ 2002 ዓ.ም

# አበርክቶ

ይህ ጥናት መታሰቢያነቱ ጅማሮዬን እንጂ ፍፃሜዬን ለማየት ላልታደሉት ወላጆቼ ለወ/ሮ አስናቀች ደምስ እና ለ) አለቃ አድማሱ ተገኝ ይሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

- ❖ ‹‹ምስጋና በሰማይ ለእግዚአብሔር ይሁን በምድርም ላይ ሰላም ለሰውም እርሱ በሚፈቅደው›› (አንቀፀ ብርሀን)
- ❖ ‹‹ቅድስት ሆይ ብፅዕት ነሽ የተመሰገንሽና የተባረክሽ ነሽ....... አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ ከተለዩ የተለየሽ የመለኮት ማደሪያ ነሽ .... ቅድስት ሆይ ልጅሽን ይቅርታ ያድለን ዘንድ ለምኚልን፡፡›› አሜን (አንቀፀ ብርሀን)
- ❖ ይህን ፅሁፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ከርዕሱ ጀምሮ ሀሳብህን በማካፈል ስህተቶችን በማረምና በማስተካከል ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ከጎኔ ሳትለይ ውድ ጊዜህን ሰውተህ ያማከርከኝ መምህር መሀሪ ዘመልአክ ስለ መልካምነትህ ቸሩ አምላክ መልካሙን ሁሉ ያድርግልህ፡፡
- ❖ ትምህርቴን ጀምሬ እስክጨርስ ያለምንም ችግር እንድማር በሞራልም ሆነ በገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከአጠገቤ ሆነህ ያበረታታኸኝ ውድ ባለቤቴ ኤፍሬም አሸብር እግዚአብሄር ይስጥልኝ፡፡ ቀሪ ዘመናችንንም ይባርክ፡፡
- ❖ ውድ ልጆቼ ቅዱስ ኤፍሬምና ንዌድስ ኤፍሬም ይህን ትምህርት ጀምሬ እስክጨርስ ለናንተ የነበረኝን ጊዜ ለትምህርቴ አካፍየዋለሁና ስለትዕግስታችሁ አመሰግናችኃለሁ፡፡ እደጉልኝ ! እግዚአብሄር አማላክ ለቁም ነገር ያብቃችሁ አድጋችሁ የቤተክርስትያን እና የሀገራችሁ አለኝታ ለመሆን ያብቃችሁ አሜን፡፡
- ❖ ይህን ጥናት በማካሂድበት ወቅት ከገበያ ውጪ የሆኑ መፅሀፍትን አፈላልገህ በመስጠት ለተባበርከኝ ለመምህር ኃ/ማርያም ላቀው ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እግዚአብሄር ጉልበትህን ይባርክ፡፡

# ማውጫ


አበርክቶ …………………………………………………………………………… I

ምስጋና …………………………………………………………………………… II

አጠቃሎ …………………………………………………………………………… III

**ምዕራፍ አንድ**

1.መግቢያ …………………………………………………………………… 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ………………………………………………………… 1

1.2. የጥናቱ አላማ ……………………………………………………… 2

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት ……………………………………………… 2

1.4. የጥናቱ ወሰን ……………………………………………………… 2

**ምዕራፍ ሁለት**

2. ክለሳ ድርሳን …………………………………………………………… 3

2.1 የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ………………………………………….. 3

2.2. የክርስቲያናዊ ግጥም የይዘት ትንተና ……………………………….. 5

2.2.1. የግጥም ምንነትና ጅማሮ …………………………………. 5

2.2.2. የክርስቲያናዊ ግጥም ምንነትና ጅማሮ …………………… 9

2.2.3. የይዘት ትንተና ……………………………………………. 13

**ምዕራፍ ሦስት**

3. የግጥሞቹ የይዘት ትንተና ……………………………………….. 15

3.1.ለእግዚአብሔር የቀረቡ ግጥሞች…………………………………… 16

3.1.1. የምስጋና ግጥሞች ……………………………………….. 16

3.1.2. የልመና ግጥሞች………………………………………….. 19

3.1.3. የንስሀ ግጥሞች…………………………………………… 20

3.1.4. የስብከት ግጥሞች………………………………………… 22
3.2. ለድንግል ማርያም የቀረቡ ግጥሞች……………………………. 24
3.2.1. የምስጋና ግጥሞች …………………………………… 25
3.2.2. የስብከት ግጥሞች …………………………………… 28
3.3. ለቅዱሳን መላዕክት የቀረቡ ግጥሞች………………………… 31
3.3.1. የልመና ግጥም……………………………………….. 31
3.4. ለቅዱሳን አባቶች የቀረቡ ግጥሞች…………………………… 32
3.4.1. የምስጋና ግጥም……………………………………… 32
3.4.2. የልመና ግጥም…………………………………….. 33
3.5. በመፅሀፍ ቅዱስ ተዐምራት ስለተደረገላቸው ሰዎች የተገጠመ…33
3.5.1. የምስጋና ግጥሞች………………………………….. 34
3.5.2. የንስሀ ግጥሞች……………………………………… 35
3.5.2. የስብከት ግጥሞች…………………………………… 35
3.6. ስለ ልዩልዩ ጉዳዮች የተገጠሙ……………………………….. 37
3.6.1. ስለነፍስና ስጋ ሙግት የተገጠመ ግጥም……………….. 37
3.6.2. የስብከት ግጥሞቸ…………………………………….. 38
3.6.2. የእንቢተኝነት ግጥሞች………………………………. 43
ማጠቃለያ
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው
ዋቢ መፅሀፍት
የግጥሞች ስብስብ

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በ‹‹ቬነስያና ሌሎች›› እና በ‹‹ከሰይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ሌሎች›› በሚሉት ሁለት መጽሀፎች ውስጥ ያሉትን ግጥሞች የይዘት ትንተና መስጠት ነው፡፡ ጥናቱ ሦስት ምዕራፎች ሲኖሩት ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ ሲቀርብበት ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳንን ይዟል፡፡ ምዕራፍ ሦስት ደግሞ የጥናቱ ውጤት ትንታኔዎች የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ በመጨረሻም ለጥናቱ ማጠቃለያ የተሰጠበት ክፍል አለ፡፡

ይህን ጥናት ለማሳካት የተመረጠው የአጠናን ዘዴ በገላጭ የምርምር ዘዴ ውስጥ የሚካተተው የይዘት ትንተና ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ግጥሞቹን በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ በመለየት የይዘት ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

# ምእራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥንታዊ ፅሁፍ በ ‹‹ቬነስያና ሌሎች›› እና ‹‹ከሠይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅና ሌሎች›› በሚሉት ሁለት መፅሀፎች ውስጥ ያሉትን ግጥሞች የይዘት ትንተና ይሰጣል፡፡ ጥናቱ በሶስት ክፍሎች የተከፋፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ ሲሆን ከስሩም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ እና የጥናቱ ወሰን በሚሉ ንዑሳን ክፍሎች የተከፋፈለ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በክለሳ ድርሳን አብይ ርዕስ ስር የተዛማች ፅሁፎች ቅኝት እና የክርስትያናዊ ግጥም የይዘት ትንተና የሚሉ ሁለት ንዑሳን ርዕሶችን ይዟል፡፡ በክፍል ሶስት በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ ያሉት ግጥሞች ባነሱት ጉዳይ ተከፋፍለው ይዘታቸው ይተነተናል፡፡ በመጨረሻም በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ የሚገኙ የግጥም ስብስቦችን እና ማጠቃለያ ይይዛል፡፡

‹‹ቬነስያና ሌሎች›› እና ‹‹ከሠይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅና ሌሎች››የሚሉት ሁለት መፅሀፎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና መምሪያ መንበረ ቅዱሳን ታርመውና ተስተካክለው የታተሙ ናቸው፡፡ መፅሀፎቹ የታተሙበት አላማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን የቅኔ፣የወግ፣የምሳሌያዊ ንግግር፣የስዕል፣የዜማ እና የታሪክ ሀብታም ብትሆንም፤ በአሁኑ ወቅት ይህ ሁሉ ሀብቷ እየተረሳ መምጣቱ ማኅበሩን እያሳሰበውና ከእነዚህ ሀብቶቿ ውስጥም አቅሙ የፈቀደውን ያህል በፅሁፍ በማስፈርና ለትውልድ በማስተላለፍ የበኩሉን በመስራት ከወቀሳ ለመዳን በማሰብ እንደሆነ የሁለቱም መፅሀፎች መግቢያ ይገልፃል፡፡ በመፅሀፎቹ ውስጥ ግጥሞች፣ አጫጭር ልቦለዶች፣ ምሳሌዎች፣ ወጎች፣አባባሎችና መጣጥፎች ይገኙበታል፡፡ ቀድሞ የታተመው መፅሀፍ ‹‹ቬነስያና ሌሎች›› በ1994 ዓ.ም ሲሆን ‹‹ከሠይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅና ሌሎች›› ደግሞ የወጣው በ1995 ዓ.ም ነው፡፡ መፅሀፎቹ የታተሙት በማህበረ ቅዱሳን ስር ከሚታተሙት ከ‹‹ሐመር›› መፅሄት የ ‹‹ኪነጥበብ›› አምድ እና በ‹‹ስምዐፅድቅ›› ጋዜጣ ደግሞ በ‹‹ኀብረ ነገር›› አምድ ስር የሚወጡትን የኪነ ጥበብ ስራዎች በመሰብሰብና አንዳንድ ትምህርቶችን በመጨመር ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አላማ በ‹‹ቬነስያና ሌሎች›› እና በ‹‹ከሠይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅና ሌሎች›› ሁለት መንፈሳዊ መፅሀፎች ውስጥ ካሉት አጫጭር ልብወለዶች፣ ግጥሞች፣አባባሎች፣ምሳሌያዊ አነጋገሮች እና ወጎች ውስጥ ግጥሞቹን ብቻ በመምረጥ ባነሱት ጉዳይ ከፋፍሎ ይዘታቸውን መተንተን ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚህ ጥናት ትኩረት በ ‹‹ቬነስያና ሌሎች›› እና በ‹‹ከሠይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅና ሌሎች›› በሚሉ መፅሀፎች ውስጥ ያሉትን ግጥሞች ይዘታቸውን መተንተን ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ሥራ ለሚያነቡ አንባብያን በመጽሀፎቹ ውስጥ ያሉት ግጥሞች ይዘት ምን እንደሚመስል እንዲያውቁ ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግጥሞቹን ከሌሎች ገጽታዎች አንጻር ለማጥናት ለሚፈልጉ፤ እንዲሁም በመጽሀፎቹ ውስጥ ከግጥም ውጪ ሌሎች ሥነጽሁፎች በመኖራቸው እንዚህን መጽሀፎች ከተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች አንጻር መገምገም ለሚፈልጉ አጥኚዎች ይህ ጥናት እንደ መንደርደሪያ ሆኖ ያገለግላቸዋል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

በ‹‹ቬነስያና ሌሎች›› እና በ ‹‹ከሠይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅና ሌሎች››በሚሉት መጽሀፎች የተለያዩ ሀይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች ማለትም አጫጭርል ልቦለዶች፣ ወጎች፣ መጣጥፎች፣ግጥሞች፣አባባሎች እና ምሳሌዎች ቢኖሩም የዚህ ጥናት ተኩረት ግን በግጥሞቹ ላይ ብቻ ነው፡፡ ጥናቱ ግጥሞቹን የሚያተኩርባቸው በይዘታቸው ላይ ብቻ እንጂ ከሌሎች የግጥም መስፈርቶች አንጻር አይመለከታቸውም፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ በመጸሀፎቹ ውስጥ በሚገኙ አጫጭር ልብወለዶች እና ወጎች ውስጥ ያሉትን ግጥሞች አያጠቃልልም፡፡

# ምእራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የተዛማች ጽሁፎች ቅኝት

ይህ ጥናት በሚያካሂደው በዚህ በክርስቲያናዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና ዙሪያ ቀጥተኛ ተመሳስሎ ያላቸው ጥናታዊ ጽሁፎች አላገኘሁም፡፡ ነገር ግን ከክርስቲያናዊ ግጥሞች አንጻር ሁለት ያህል ጥናታዊ ጽሁፎችን አግኝቻለሁ እነሱም

1. ወርቂቱ ቱፋ በ1997 ዓ.ም ‹‹የዘማሪ ይልማ ኃይሉ የመዝሙር ግጥሞች ላይ የይዘት እና የቅርጽ ትንተና›› እና
2. አስማረች ተሾመ በ1998 ‹‹ በሐመር መፅሄት ላይ የወጡ ግጥሞች መዘርዘር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር›› ናቸው፡፡

ወርቂቱ ቱፋ ‹‹የዘማሪ ይልማ ኃይሉን የመዝሙር ግጥሞች የይዘት እና የቅርጽ ትንተና በሚል ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለዲግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጽሁፍ የዘማሪ ይልማ ኃይሉን ዘጠኝ ካሴቶች ውስጥ የሚገኙትን የመዝሙር ግጥሞች ከቅርጽና ከይዘት አንጻር ተንትናለች፡፡ ጥናታዊ ፅሁፉ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በጥናቱ መግቢያ ላይ የሥነ-ግጥምን ምንነት በመግለጽ መንፈሳዊ ግጥም ከይዘቱና ከአላማው ውጪ ከሌላው ግጥም ጋር አንድ አይነት መሆኑን ገልፃለች፡፡ ወደ ጥናቷ ስትገባ በክፍል አንድ መግቢያና የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት አቅርባለች፡፡ በክፍል ሁለት መዝሙር ግጥም ምንነት፣ መዝሙር በቤተ ክርስትያን ያለውን አገልግሎት፣ መዝሙራቱ የሚዘመርባቸው አጋጣሚዎች፣ መዝሙራቱ የሚዘመሩበት መንገድ፣ የቤተ ክርስትያን መዝሙር መሳሪያዎች እና የመዝምራቱ አጠቃላይ ገጽታ ዛሬ የሚሉ ሀሳቦችን አስተናግዳለች፡፡ ክፍል ሶስት በዘጠኙ ካሴቶች ውስጥ ካሉ ዘጠና ሁለት መዝሙሮች አርባ ሁለት በመምረጥ በይዘታቸው አንጻር በመከፋፈል ትንተና አቅርባለች፡፡ በክፍል አራት በግጥሞቹ ቅርጽ የተተነተኑበት ክፍል ሲሆን ቅርጽን በሁለት በመክፈል ከውስጣዊና ከውጫዊ ቅርጽ አንጻር ግጥሞቹ ምን

እንደሚመስሉ በምሳሌ በማስደገፍ ገልጻለች፡፡ በመጨረሻም የመፍትሄ ሀሳቦችንና ማጠቃለያ ሰጥታለች፡፡

የወርቂቱ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ዋነኛው ጉዳይ በሁለቱም ጥናቶች ውስጥ የሚነሳው የኦርቶዶክሳዊ ግጥሞች የይዘት ትንተና መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ግጥሞቹ ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳዮች አንጻር ተከፋፍለው መጠናቸው ያመሳስለዋል፡፡ ይህ ጥናት ከወርቂቱ ጥናት የሚለየው እርሷ በጥናቷ የመዝሙር ግጥሞችን ከቅርጽ አንጻር ትንተና ሰጥታለች በዚህም ጥናት ግን የይዘት ትንተና መስጠት እንጂ የቅርጽ ትንተና አይካተትም፡፡

ወርቂቱ በጥናቷ መጨረሻ የመፍትሄ ሀሳብ አቅርባለች ችግሩን ሳትገልፅ በደፈናው ‹‹ብዙ ማስተካከል የሚገባቸውን ነገሮች አግኝቻለሁ›› ከማለት ውጪ ችግሩን ተንትና ለማስረዳት አልሞከረችም ስለሆነም ለየትኛውም መዝሙር ግጥም መፍትሄ እንደሰጠች ግልጽ አለመሆኑ በዚህ ጥናት አቅራቢ ሳይጠቅስ አያልፍም፡፡

ሌላው ጥናት የአስማረች ተሾመ በ1998 ዓ.ም ‹‹በሐመር መጽሄት ላይ የወጡ ግጥሞች መዘርዘር ከአጭር መግለጫዎች ጋር›› የሚለው ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ አጥኚዎ ከ1985 እስከ 1989 ዓ.ም በሐመር መጽሄቶች ላይ የወጡ ግጥሞች አጫጭር መግለጫ ሰጥታለች፡፡ ጥናታዊ ጽሁፏ እንደ ወርቅነሽ ሁሉ አራት ክፍሎችን ይዟል፡፡ በክፍል አንድ የጥናቱ አላማ፣ አነሳሽ ምክንያት ፣የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰንና የአጠናን ዘዴ ያካትታል በክፍል ሁለት የተዛማች ጽሁፍ ቅኝት እና ስለ ሐመር መጽሄት መታተም ዓላማ፣ አጀማመር እና እድገት መዘርዝር እና አጫጭር መግለጫ ከንድፈ ሀሳባዊ ብያኔ ጋር ሰጥታለች፡፡ በክፍል ሶስት ከ1998 እስከ 1989 ዓ.ም ሐመር መጽሄት ላይ የወጡ ግጥሞችን የመልእክታቸውን ምንነት እና መቼ እና በማን እንደተፃፉ በመግለፅ የግጥሞቹ መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር ቀርበዋል ፡፡በክፍል አራት ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

የአስማረችና ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የሚያመሳስለው ዋነኛውና ብቸኛው ጉዳይ በሁለቱም ጥናቶች መንፈሳዊ ግጥሞችን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው ነው፡፡ የሚለያዩበት ደግሞ የዚህ ጥናት ትኩረት በግጥሞች ላይ የይዘት ትንተና መስጠት

ሲሆን የአስማሪች ጥናት ትኩረት ደግሞ የግጥሞቹን ስብስብ ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር ማቅረብ ነው፡፡

## 2.2 የክርስትያናዊ ግጥም የዘት ትንተና

### 2.2.1. የግጥም ምንነትና ጅማሮ

‹‹ግጥም›› የሚለው ቃል ፅንሰሀሳብ ‹‹ሥነግጥም›› ከሚለው ቃል ፅንሰሀሳብ ጋር ያለው ፍቺ በአንዳንድ ፅሁፎች ውስጥ ለመለየት አስቸጋሪ ነው፡፡ ቃላቱ የትርጉም ለውጥ እንደሌላቸው ሁሉ ሁለቱም ለተመሳሰይ ፅንሰሀሳብ መግለጫነት ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡ የእነዚህን ቃላት የፅንሰሀሳብ ልዩነት ብርሀኑ ገበየሁ ‹‹ የአማርኛ ስነግጥም›› በተሰኘው መፅሀፉ እንደሚከተለው ይበይነዋል፡፡

‹‹ግጥም፡- በቋንቋ አጠቃቀማቸው፣ በቅርፃዊ መዋቅራቸው፣ በዜማ ስልታቸው ተለይተው የሚታወቁ የጥበብ ስራዎች ጥቅል መጠሪያ ስያሜ ነው፡፡ ስያሜው በተለይ ለአንድ ቅንጣት (ነጠላ) የጥበብ ስራ መጠሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

‹‹ሥነ-ግጥም፡- እንደ ጥናት መስክ መጠሪያ፣ ስለ አገጣጠም ብልሀትና ስልት፣ ስለግጥም ቅርፃዊ ገፅታዎች እንዲሁም ስለግጥም አተናተንና አተረጓጎም የሚያጠናው ትምህርት ዘርፍ መጠሪያ ስያሜ ነው፡፡

እንዲሁም ስነግጥም እንደ ጥበባዊ ስራዎች ጥቅል መጠሪያ በአገጣጠም ስልታቸው ጥልቅነትና ልቀት ተለይተው የታወቁና የተመሰከረላቸው የአንድ ወይም የበርካታ ገጣሚያን ሥራዎች የጥቅል መጠሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ (ብርሀኑ 1999 ገጽ 3-4)

ስለ ግጥምና ሥነግጥም ፅንሰሀሳብ ይህን ያህል ግንዛቤ ካገኘን የግጥምን ምንነት እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

‹‹ግጥም ከኪነጥበብ ስራዎች አንዱ ነው፡፡ ስለግጥም የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔን ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን እንመልከት፡፡

- ዘሪሁን አስፋው ‹‹ የስነፅሁፍ መስረታውያን›› በተሰኘው መፅሀፋቸው ግጥም ምንድር ነው ለሚለው ጥያቄ አጭር ብያኔ መስጠት አለመቻሉን እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> ‹‹በኪነጥበብ ዘመን ታሪክ፡ ብዙ የኖረ በመሆኑ እንደዘመኑ ፍልስፍና፣ እንደዘመኑ ገናና የኪነጥበብ ፈለግ፣ እንደየገጣሚው፣ እንደየፍልስፍና አዋቂው አተያይና የኪነጥበብ ዝንባሌ የተለያዩ ብያኔዎች ሊሰጡት ቆይተዋል፡፡ … ግጥምን ይበልጥ ለመረዳት የተሻለ ዘዴ በአጭር ብያኔ ከመወሰን የቅርፅና የይዘት ባህሪያቱን በውል መገንዘብ ነው፡፡›› (ዘሪሁን ፣1992 ÷ 73)

በማለት የተሻለ የሚሉትን ኃሳብ በመጨመር ገልፀዋል፡፡

- ሰለሞን ደሬሳ ‹‹ልጅነት›› በሚለው የግጥም መፅሀፉ መግቢያ ላይ

> ‹‹የግጥም ፈንታ የሰው ልጅ [የኑሮ አላማውምውን ለማሳካት የሚያደርገውን ] ግላዊ መፍጨርጨር… ከዚህም አለም ችላ ባይነት ጋር አያይዞ ማብላላት ይመስለኛል፡፡ ማብላላት፣ ማፏጨት፣ እያፏጨ ተቃራኒዎችን ማጣመድ፣ ተመሳሳዮችን ማለያየት፡፡ ከግጭታቸው ለአንዳፍታ እንደ በራሪ ኮከብ የሚታይ ግልጥ መፍትሄ ማዋለድ…›› (ሰሎሞን ፣ 1963)

በማለት ስለግጥም የሚሰማውን ይገልጻል፡፡

- ፀጋዬ ገብረ መድህን እሳት ወይ አበባ በተሰኘው የግጥም በድብሉ መግቢያ ላይ

> ‹‹ በቃለ ውበቱና በቃለ ኃይሉ ፤ ወይም በድቀቱ ስምረት ለአዕምሮ፣ ለልቦናና ለስሜት የሚመስጥ ባለስልትና ባለድንጋጌ የቋንቋ አደራደር ሁሉ ሥነ-ግጥም (ፓኤተሪ) ይሉታል፡፡›› (ፀጋዮ፣1996 ፣ 7)

በማለት ብያኔ ይሰጣል፡፡

- ኃይሉ ገ/ዮሐንስ የተባለው ገጣሚ ደግሞ ግጥምን እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡፡

‹‹የአካባቢ ልዩ ኃይሎች በመንፈስ ላይ በሚያሳድሩት ተጽእኖና በሚያስከትሉት ይህሊና ጭንቀት፣የተለየ ሀሳብ በልቦና ውስጥ ይጸነሳል፡፡ ያም ጽንሰሀሳብ ሲብላላና ሲጋጋል ከቆየ በኋላ በልዩ ልዩ መልክ በአንደበት በኩል ይፈነዳል፡፡ አንደበት ኃሳብን ከሚገልፅባቸው አይነቶች አንደኛው ግጥም ነው፡፡›› (ገሞራው፣1996፣ በረከተ መርገምተ)

- አያልነህ ሙላቱ የግጥምን ምንነትና ከሌሎች የሥነፅሁፍ ዘርፎች የሚለይበት ሲገለጽ

‹‹ ግጥም ጥልቀት ያለው ኃሳብ፣ እጥር ምጥን ባሉ የተዋቡ ቃላት የሚገለጽበት የሥነ-ፅሁፍ ዘርፍ ነው፡፡ ከልቦለድ የሚለየውም፣ ማራኪና ውብ ምርጥ የሆኑ ቃላት ምታዊ ድርደራ የሰውን ልጅ ውስጣዊ ስሜት ጠልቆ በመግባት ህልሙንና ስብዕናውን ለመግለጽ በመቻሉ ነው፡፡ ግጥም የዕውነት ነጸብራቅ  የህይወት ኃያሲና ተምሳሌትም ነው፡፡ የጠራ መንፈስ የሚገለጽበት እስትንፋስም ነው፡፡ አልፎ አልፎም ግብታዊ በሆነ ስሜት የሚፈልቅ የሀሳብ ምንጮች የሚፈሱበት የጥበብ ቃሊም ነው፡፡›› (አያልነህ፣1984 ፣ማን ይሆን የበላ?)

- አለማየሁ ሞገስ ደግሞ ‹‹ የአማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማሪያ›› በሚለው መጸሀፋቸው ‹‹ ማንኛውም ዝርው ቤት እየመታ በስንኝ ተሳክቶ ሲነገር ግጥም ይባላል፡፡››(አለማየሁ፣ 1954 ፣7) በማለት የግጥም ብያኔ ሰጥተዋል፡፡
- በማኅበረ ቅዱሳን አባላት የተጻፈው ‹‹ ኦርቶዶክሳዊ ስነፅሁፍ›› የሚለው ጽሁፍ ስለ ግጥም ምንነት ሲገልጽ እንደሚከተለው ብሏል ፡፡

‹‹ ግጥም የራሱ የሆነ ቅርጽ እና ይዘት አለው፡፡ ይህም የሚዳሰስ ባይሆንም የስንኞቹ መገናኘት፣ የድምጽ ስልት አወራረድ ፣ከቃለቱ የሚፍለቀለቁ የስእሎች አመጣጥ፣ በወረቀቶች ላይ ታትሞ የሚታየው የመስመሮች ርዝመት የሚፈጥረው የሀሳብ እና የዜማ መወሳሰብ ነው፡፡ ግጥም የራሱ የሆነ ሕግና ስርዐት አለው፡፡ በውበት ደረጀ እንዲቀርብ ከማስፈለጉም በላይ የምጣኔ ቀለሞች፣ የሀረግ፣የስንኝ በተለይም የዜማ ባህርያት በጥንቃቄ መለካት ይኖርባችኋል፡፡ እነዚህን አሟልቶ ካልተገኘ ለማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት ሳይተላለፍ ሊቀር እንደሚችል መገመት አያስቸግርም ምክንያቱም

በሳል ግጥም የሚያሰኘው የእነዚህ ባህርያት የጠበቀ ቁርኝት እና አንድነት በውል ተጣምረው የሚያስገኙት ኃይል ነው፡፡››(ገፅ 9)

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሰው ብያኔ ግጥም የራሱ የሆነ ቅርጽ፣ ይዘት፣ ህግና ስርአት እንዳሉትና እነዚህንም ጠብቆ ያልተፃፈ ግጥም ግቡን ሊመታ እንደማይችል ይገልጻል፡፡

ወርቂቱ ቱፋ ‹‹ የዘማሪ ይልማ ኃይሉ የመዝሙር ግጥሞች ይዘት እና ቅርጽ ትንተና›› በሚለው ጥናታዊ ጽሁፏ ግጥምን ‹‹የሰው ልጅ በገሀዳዊ አለም የሚገጥመውን የኑሮ ውጣ ውረድ ከሰው አዕምሮ ውስጥ ምስልን ሊፈጥሩ በሚችሉ የተመረጡ ቃላት የሚቀርብ አልፎም በቃልም ሆነ በጽሁፍ ሊቀርብ የሚችል የኪነ-ጥበብ ዘር ነው፡፡›› (ወርቂቱ፣1997) በማለት ትገልፃለች፡፡

ከላይ ስለግጥም ምንነት የተለያዩ ፀሀፊያን አስተያየት መሰረት በማድረግ ለመግጽ ተሞክሯል አሁን ደግሞ የግጥምን አጀማመር ለማየት እንሞክር ፡፡

የሰው ልጆች ሀሳባቸውን በፅሁፍ መግለጽ ከመጀመራቸው በፊት በቃል ግጥም ሀዘናቸውን ፣ደስታቸውን፣ ብሶታቸውን፣ምኞታቸውን ወዘተ… ይገልፁ እንደነበር ፅሁፎች ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም ግጥም ቋንቋ ሲፈጠር አብሮ የተፈጠረ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በመሆኑም ግጥም እጅግ ጥንታዊነቱ የሚነገርለት የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በራሷ ቋንቋና ፊደል በመፃፍ ቀዳሚት ሀገር እንደሆነች ይልማ ከበደ ‹‹የአማርኛ ስነ-ግጥም 1307 እስከ 1933) በሚለው መጽሀፉ ይገልጸዋል፡፡ (ይልማ፣1982፣1) በመቀጠልም፤ የግእዝ ቋንቋ እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብቸኛው የሀገሪቷ የፅሁፍ ቋንቋ በመሆኑ ብዙ ጥንታዊ ቅኔዎችም በዚሁ ቋንቋ መጻፋቸውን በመግለጽ ከሰባተኛው ምእት አመት በኋላ ግን አማርኛ የግእዝ ቋንቋን እየተጋፋ እንደመጣ በተለይም በ14ኛው ምእት አመት የመጀመሪያው አጋማሽ ላይ የነገስታት የውዳሴ ግጥሞች በአማርኛ መፃፋቸውን ያትታል በግጥሞቹም ዙሪያ በዘመን ቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው አጠር ያለ አስተያየት ይሰጣል፡፡

1. **ለአፄ አምደ ፅዮን የተፃፈ የምስጋና ግጥም (1307-1313**)

ይህ ግጥም አምደ ፅዮን የእስልምና ሐይማኖት አስፋፊዎችንና በሀገሪቱ ውስጥ የተነሱትን አመፀኞች ድል እንዳደረጋቸው የሚነግር እንደሆነ ገልፆ፤ ያገጣጠሙን ስልት ሂደት በመመርመር ምንአልባት ገጣሚው በግእዝ ቅኔ ትምህርት ያልተገራ ተራ የንጉስ አምደ ፅዮን አጃቢ ሲሆን ግጥሙም ስሜቱን ለመግለጽ በተራ ቋንቋ የጻፈው ግጥም ነው ለማለት ይቻላል ብሏል፡፡

2. **ለአፄ ዳዊት የተፃፈ የምስጋና ግጥም (1375-1404)**

የዚህ ግጥም ዋና መልእክት በሀገሩ ውስጥ የነበሩ አመፀኞች ለአፄ ዳዊት አንገብርም ባሉ ጊዜ ንጉሱ ድል እንዳደረጋቸው እና የንጉሱን ጀግንነት፣ ሀያልነት እና አስፈሪነት እንዲሁም የአመፀኞቹን ጭንቀት የሚያስረዳ ነው፡፡ ይህ ግጥም በርከት ያሉ ለዘመናችን ቅርብ የሆኑ አማርኛ ቃላት እና የሰዋሰው አወቃቀር ጎላ ብሎ ይታይበታል ግጥሙም ከአፄ አምደ ፂዮን የምስጋና ግጥም አፃጻፍ ስልት የጎላ ልዩነት አይታይበትም በማለት ጽሁፉ ያስረዳል፡፡

3. **ለአፄ ይስሐቅ የተፃፈ የምስጋና ግጥም (1407-1422)**

ስለአፄ ይስሐቅ የተፃፉ ሁለት የምስጋና ግጥሞች ተገኝተዋል እነዚህ ግጥሞች በዘይቤ መልእክትን አግዝፎ እና አድምቆ በማቅረብ ከሌሎቹ ይልቅ ጎልተው ይታያሉ፡፡ በዘመኑም ለመጀመሪያ ጊዜ የታየ ከፍተኛ የአጻጻፍ ጥበብ በእነዚህ ግጥሞች ታይቷል፡፡ የሚል አመለካከት አለው

4. **ለአፄ ዘርዐያእቆብ የተፃፈ የምስጋና ግጥም (1426-1460)**

የግጥሙ መልእክት የንጉሱን አስደንጋጭንት፣መልከመልካምነት፣ ጀግንነት ወዘተ በሌሎች ዘንድ እንዲታወቅ የሚያደርግ እንደሆነ ይግልጻል፡፡

5. **ለአፄ ገላውዴዎስ (አጥናፍሰገድ)የተፃፈ የምስጋና ግጥም (1532-1551)**

የዚህ ግጥም ዋና መልእክት ንጉሱ ግራኝን ድል አድርጎ የተዋህዶ ሐይማኖት እንዲያንሰራራ በማድረጉ ለውዳሴ የቀረበ ግጥም ነው፡፡ ግጥሙ ከአሁን ቀደም ከተፃፉት ይበልጥ በቃላት እና በሰዋሰው አገባብ ለዘመናችን እጅግ የቀረበ ነው፡፡ በአንድ ሆሄ ድምጽ ብዙ ስንኞች ቤት እንዲመቱ መደረጉ ከቀደሙት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በማለት ይልማ ከበደ ያትታል (ይልማ፣1982፣1-12)

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው የአምስት ነገስታት የውዳሴ ግጥሞች የአማርኛ ግጥምን ጥንተ አመጣጥ በመጠኑም ቢሆን አስገንዝበናል፡፡ ምንም እንኳን የአማርኛ ስነ-ፅሁፍ በእነዚህ ግጥሞች ይጀመር እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ክርስቲያናዊ ግጥሞች ጅማሮ በግእዝ ቅኔ እንደሆነ ከላይ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ ግእዝም እስከ አሁን ድርስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን የምትገለገልበት ቋንቋ ነው፡፡ ጥንታዊውም ስነ-ፅሁፍ በክርስትና እምነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፤ በኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ ግጥም እጅግ ጥንታዊ ነው ማለት እንችላለን፡፡ በአለም ደረጃ የክርስቲያናዊ ግጥምን አመጣጥ በአጭሩ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

### 2.2.2 የክርስቲያናዊ ግጥም ምንነትና ጅማሮ

ክርስቲያናዊ ግጥም ማለት ምንጊዜም ምንጩ መፅሀፍ ቅዱሳዊ የሆነ ክርስትናን የሚያስተምር መልእክት ወይም መግለጫ ያለው ማኘኛውም ግጥም ነው፡፡ በማለት wikipedia the free encyclopedia ብየኔ ይሰጣል፡፡

‹‹ኦርቶዶክሳዊ ስነ-ፅሁፍ›› በሚል በማህበረ ቅዱሳን አባላት የተፃፈው ጽሁፍ ደግሞ የክርስቲያናዊ ግጥምን ሲገልጽ

> ‹‹ ክርስቲያናዊ ግጥም ስለአንድ ጭብጥ ነገር አድምቆ እና አጉልቶ የማሳየት ችሎታ ያለው በጥቂት ምርጥ ቃላት ብዙ መልእክትን ማስተላለፍ የሚችልና ነግሮችን አምቆ የመያዝ ችሎታ የለው ነው፡፡ በተለይ ኦርቶዳክሳዊ ግጥም ባለው ስርዐታዊ አደራደርና ስሜት ሰጪነት የላቀ መንፈሳዊ መልዕክትን የማስተላለፍ ባህሪው ከፍተኛ መሆኑ በአያሌው ይነገርለታል፡፡ ይኸውም ከቁጥብነትና ከእምቅነት ባህሪው የተነሳ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ክርስቲያናዊ ግጥም አእምሮአዊ፣ ስሜታዊ ምናባዊ ከመሆኑም በላይ እንደሌሎቹ ክርስቲያናዊ ስነ-ፅሁፍች ትኩረቱ በክርስቲያኖች ህይወት ላይ ነው፡፡በክርስትና ሕይወት ያለውን ውጣ ውረድ ወይም ወድቆ መነሳት እና የመሳሰሉትን ፀሀፊው በምልከታ የታዘበውን ልቡ ያረፈበትንና ስሜቱ የቆጠቆጠውን መርጦ በራሱ ፈጠራ አዋቅሮ አቀናጅቶ ውለኛ ትርጓሜ በመስጠት ለአንባቢ ያቀርባል፡፡›› (ገጽ 7) በማለት ሰፋ ያለ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

ከላይ ለማየት ከሞከርናቸው ብያኔዎች በመነሳት ክርስቲያናዊ ግጥም ከይዘቱና ከአላማው በስተቀር በሌሎች የግጥም መስፈርቶች አንጻር ሲታይ፣ ማለትም

በአደራደሩ፣ በውስጣዊ መዋቅሩ፣ በምጣኔና ምቱ፣ በቤት አመታቱ በአጠቃላይ በአሰኘኙቱ ከሌላ ግጥም ጋር አንድ አይነት ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ስለክርስቲያናዊ ግጥም ብያኔ ይህን ያህል ከጠቀስን ስለአጀማመሩ ጥቂት እንበል፡፡ ክርስቲያናዊ ግጥም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በትክክል በዚህ ዘመን ተጀመረ ለማለት ቢያስቸግርም እጅግ ጥንታዊነቱ የሚነገርለት የኪነጥበብ ዘርፍ መሆኑ እውን ነው፡፡ ስለክርስቲያናዊ ግጥም አጀማመር wikipedia the free encyclopedia እንደሚከተለው ያትታል፡፡

ክርስቲያናዊ ግጥም የክርስትና ታሪክ በጽሁፍ መልክ መፃፍ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ይፃፍ ነበር፡፡ በእርግጥ ጥንታዊው ክርስቲያናዊ ግጥም በአዲስ ኪዳን ታይቷል፡፡ magnificat እና Nunc የተባሉ በሀዲስ ኪዳን ግጥሞች ተፅፈዋል፡፡ በተጨማሪም ብዙ የመፅሀፍ ቅዱስ ምሁራን የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች ምዕራፍ 2÷5-11የተፃፈውን ፅሁፍ በመጥቀስ የዘመኑ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ መዝሙሮችን እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የክርስቲያን ገጣሚዎች ከግሪክ እና ከላቲን ባዕድ አምላኪዎች ባለቅኔዎች ፅምነት ጋር ትምህርታቸውን አገናኝተው ለመጻፍ ይጥሩ ነበር በማለት ፅሁፍ የሐዋሪያት ስራን ምዕራፍ 17÷28 ያለውን እንደ ምሳሌ ይጠቅሳል፡፡ ይኸውም ሐዋሪያው ጳውሎስ ለአቴና ሰዎች የሰበከላቸውን ነው፡፡ ቃሉም እንዲህ ይላል፡፡ ‹‹ ከእናንተ ከባለቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ፡- እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደተናገሩ ለእርሱ ህያዋን ነንና ››እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን፡፡››የአቴና ባለቅኔዎች ‹‹እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና›› ብለው ያሉት አምላካቸው ወይም ከአማልክታቸው ለአንዱ ሲሆን ቅዱስ ጳውሎስ ግን ይህን እያወቀ እግዚሐብሔርን እንዳሉ፣ ያሉትም ትክክል እንደሆነ ይነግራቸዋል፡፡ ከዛም በመቀጠል ‹‹እንግዲህ የእግዚሐብሔር ዘመዶች ከሆንን አምላክ በሰው ብልሀትና ሀሳብ የተቀረፀውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባም›› በማለት በጥበብ የጣኦታትን አምልኮ በመተው ክርስትናን እንዲቀበሉ ይሰብካቸዋል፡፡

እንደዚሁም ሁሉ አንዳንድ ጥንታዊ የክርስቲያን ገጣሚያን ግጥማቸው ባዕድ አምልኮን የሚያወሳ እና የጥንታዊ ግሪኮችንና ሮማዎችን ጥንታዊ የፅሁፍ ቅርፅ ይዞ እንዲቀጥል

አድርጓል፡፡ ሌሎች ክርስቲያናዊ ግጥሞች የግሪክ አፈታሪኮችን ትተው የአጻጻፍ ቅርጻቸውን ብቻ በመውረስ ቀጥለዋል፡፡ ሌሎች ጥንታዊያን የክርስትያን ግጥም ፀሐፊያን ደግሞ አዳዲስ የአፃፃፍ ቴክኒኮችንና ሀሳቦችን ፈጥረው በመጠቀም አስተዋውቀዋል፡፡ እነዚህ ገጣሚያን ብዙና ጠቃሚ የሆኑ መንፈሳዊ ግጥሞችን ፅፈዋል፡፡ ግጥሞቹም እስከ አሁን ድረስ በሮም ካቶሊክ ቤተክርስትያን ስርአት ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ በማለት ፅሁፉ ያትታል በመቀጠልም በስነፅሁፍና በስነልሳን አጥኚዎች አተያይ እነዚህ ግጥሞች ጠቃሚ የሆኑ ቲክኒኮችንና ሀሳቦችን በማመልከታቸው ከእነርሱ በኋላ ለተነሱ ገጣሚያን የግሪክን የግጥም መፃፊያ ህግና የሮማውያንን አፈ-ታሪክ እንዲሁም ወታደራዊ መዝሙሮችን መሰረት ከማድረግ እንደገላገሉዋቸው ይናገራሉ፡፡

ጥንታዊው የእንግሊዘኛ ክርስቲያናዊ ግጥም ‹‹ The Dream of the Road›› የሚለው ሲሆን ይዘቱም የክርስቶስን ስነ-ስቅለት በጥልቀት የሚያሳይ ነው ይለናል ጽሁፉ በመቀጠልም ለእንግሊዝ ጥንታዊ ስነ-ፅሁፍ ከጥነታውያኑ ግጥሞች አሁን ሊገኝ የቻለ ታላቅ ቅርስ እንደሆነ ይገለፃል፡፡ ሌላው ከጥንታዊ ጽሁፎች ውስጥ የሚነሳው የDante Alighieri << The Divine Comedy>> የሚባለው ሲሆን ግጥሙ ለኢጣልያ ስነፅሁፍ ቅርስ እንደሆነ ያነሳል ፡፡ በጣም ጥንታዊ የሆነው የአይርላንድ ክርስቲያናዊ ግጥም ሲሆን ስራውም የአየርላንድ መነኮሳት ነው፡፡ ይህም ግጥም ሐይማኖታዊ መልእክት ያዘለ ነው፡፡ የዚህ ግጥም ታሪክ በብዙ የአውሮፓ ቋንቋዎች ይነገራል በማለት ጽሁፉ ያትታል፡፡

ስለክርስቲያናዊ ግጥም አነሳስ የሀገራችን ጸሀፊያን ያሉትን ደግሞ እንደሚከተለው እንይ

በማኅበረ ቅዱሳን አባላት የተጻፈው ‹‹ኦርቶዶክሳዊ ስነፅሁፍ›› የተሰኘው ፅሁፍ ስለክርስቲያናዊ ግጥም ጅማሮ እንደሚከተለው ብሏል

> ‹‹የመዝሙር ድርሰቶች የሚፃፉት በግጥም መሆኑ ይታወቃል በዘፀ 15 እና 16 እንደምናነበው እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ያወጣቸውን እግዚሕአብሔር አምላክን ለማመስገን ዘምረዋል፡፡ የነብዩ ዳዊትም መዝሙር የተፃፈው በግጥም መልክ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ከቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰት አስቀድሞ የግጥም ድርሰት እንደነበረና የቅዱስ ያሬድ የድጓ ድርሰትም እነዚህን ድርሰቶች መሠረት ያደረገ መሆኑን ይነገራል መልከአ

መልኮች የተፃፉትም በግጥም ነው፡፡ በዘመናችንም በአበይት በአላትና በንግስ ጊዜ የሚዘመሩ የቅዱሳን ሰማእታትን ተጋድሎ የሚያሳዩ የቅዱሳን መላእክትን ተራዳኢነትና ጠባቂነት የሚያመለክቱ እንዲሁም የእመቤታችን የቅድስት ማርያምንና የአምላክ ምስጋና መዝሙሮች ስነቃላዊ ትውፊቶች ናቸው፡፡›› (ገጽ 6-7)

ስለክርስቲያናዊ ግጥሞች ጥንት አመጣጥ ይህን ያህል ካልን በክርስቲያናዊ ግጥሞች ውስጥ የቃላት ምርጫ፣ ምሳሌ እና የዘይቤ አጠቃቀም ምን እንመሚመስል በጥቂቱ ለማየት እንሞክር

**የቃላት ምርጫ** ፡- ለግጥም ከጠበቀ ምቱና ከምጣኔው በተጨማሪ የቃላት መርጫ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ ግጥም ከዝርው ይልቅ ምርጥ ቃላትን የሚፈልግ የስነፅሁፍ ዘርፍ ነው፡፡ የግጥሙን ይዘት በመረዳት እናገኘዋለን እንጂ ገጣሚው መልእክቱ ይህ ነው ብሎ አያመለክተንም፡፡ የገጣሚው ድርሻ ሀሳቡን መግለፅ የሚያስችሉትን ቃላት በመጠቀም አንባቢው እንዲረዳው ማድረግ ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊ ስነጽሁፍ ስለክርስቲያናዊ ግጥም የቃላት መርጫ ሲገልጽ

> ‹‹ ክርስቲያናዊ ግጥምም እንደሌላው ግጥም ሁሉም ምርጥ ቃላትን ይሻል፡፡ በተለይ ኦርቶዶክሳዊ ግጥም ከቁንጥብጥብነቱ ከእምቅነቱ ሌላ ምስጢር አዘል መሆን ስላለበት ምርጥ እና የቤተክርስትያን ለዛ ያላቸውን ቃላት ሊጠቀም ይገባል፡፡ በተመረጡት ጥቂት ቃላት ከሰው ልብ ዘልቆ በመግባት ሰውን ለንስሀ እንዲዘጋጅ፣ የሰማይ ቤቱን እያሰበ ለፅድቅ እንዲተጋ፣ ከበደል እንዲርቅ ማድረግ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡›› በማለት ያትታል፡፡

**ምሰላ**፡- ገጣሚው ለማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት ለአንባቢው ወይም ለአድማጩ በጉልህ እንዲታይ አድርጎ ለማቅረብ በግጥሙ ውስጥ ምሰላን ይጠቀማል፡፡ በምሰላ አንድን ነገር ቀርጹንና ቀለምን ስፋትና ጥበትን በግልጽ እንድንመለከት ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ክርስቲያናዊ ግጥሞች ውስጥ በምሰላ የተፃፈ ግጥሞችን እናገኛለን፡፡

**የዘይቤ አጠቃቀም**፡- ዘይቤ የአንድን ነገር ባህሪ ወይም ድርጊት ከሌላ ነገር ባህሪ ወይም ደርጊት ጋር በማወዳደር ፣ በማመሳሰል፣ አንዱን ከሌላው በመወከል ነገሮች አጉልቶ ለማሳየት የሚረዳ ነው፡፡ በክርስቲያናዊ ግጥምም ሁሉንም አይነት ዘይቤዎች መጠቀም ይቻላል፡፡ በአብዛኛው ክርስቲያናዊ ግጥሞች ውስጥ በተለይ ተነፃፃሪ እና ተለዋጭ ዘይቤዎች ይገኛሉ፡፡

## የይዘት ትንተና

የአንድ ጽሁፍ ይዘት እንደተደራሲው እይታ የተለያዩ ፍቺ ሊሰጠው ይችላል፡፡ የአንድ ሰው እይታ ከሌላ ሰው እይታ ፍፁም ሊመሳሰል ወይም ፍጹም ሊለያይ ይችላል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሰዎች ነገሮችን የሚያገናዝቡበት መንገድ እንደየእድሜአቸው፣ እንደየእውቀተቃቸው፣እንደየተሰጥኦአቸው የተለያየ መሆኑ ነው፡፡ ይህን እንደመነሻ ይዘን የተለያዩ ምሁራን ስለይዘት ትንተና ያሉትን እንመልከት

- ደረጀ ገብሬ የስነ አእምሮ መዝገበ ቃላትን በመጥቀስ እንዲህ ብለዋል ‹‹ የይዘት ትንተና የተለያዩ ጭብጦችን የያዙ የሰነዶች መልእክቶችን፣ ሀሳቦችን ፣ ስሜቶችንና አስተያየቶችን የሚተነትኑባቸው የተለያዩ ዘዴዎችን የሚያቅፍ ነው፡፡ (ደረጀ 1986፣ገጽ 30)
- የይዘት ትንተና ማለት አንድን ጽሁፍ በጥሞና ካነበብን በኋላ የምንደርስበት መደምደምያ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አንድን ጽሁፍ ለመፃፍ መክንያት የሚሆነው አስኳል ጉዳይ የይዘት ትንተና ነው ማለት ይቻላል፡፡ የሚል ሀሳብ ያላቸው እነ Philips J.Ston የይዘት ትንተናን ሲበይኑ ‹‹ይዘታዊ ትንተና በማንኛውም ጥናት ውስጥ ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ የተወሰኑ ባህርያትን በመለያየት ስርአታዊና ያልተዛባ መደምደሚያ ላይ መድረሻ ዘዴ ነው፡፡ ‹‹( Philips 1966 P.5)›› በማለት ይገልፃሉ፡፡

## የክርስቲያናዊ ግጥም ይዘት ትንተና

ክርስቲያናዊ ግጥም ይዘት ሐይማኖታዊ መሆን እንዳለበት ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የክርስቲያናዊ ግጥሞች ይዘት ከሌሎች ግጥሞች ይዘት የተለየ ነው፡፡

ስለመንፈሳዊ ግጥም ይዘት ወርቂቱ ቱፋ ‹‹የዘማሪ ይልማ ሀይሉ የመዝሙር ግጥሞች የይዘት ትንተና›› በሚለው ጥናታዊ ፅሁፏ እንዲህ ብላለች፡፡

> ‹‹በግጥም ውስጥ ይዘት የምንለው በቃላቱ በዘይቤአዊ አነጋገሩ ፣በምናብ አሳሳሉ እና በአጠቃላይ ለግጥሙ ውበትን በሚሰጡ መለኪያዎች አማካኝነት የሚተላለፈው የግጥሙ ቁምነገር ነው፡፡ ይህም የሚተላለፈው ቁም ነገር በሁለት መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አንደኛው በጽሁፉ ወይም በግጥሙ ውስጥ ያለው አጠቃለይ እውነታ ሲሆን ሌላው ደግሞ ግጥሙ በዚያ በተወሰነ ጽሁፍ የሚያስፈልገው አንድ የተወሰነ ጭብጥ ነው፡፡›› (ወርቂቱ ፣1997)

ክርስቲያናዊ ግጥም ትኩረት ተሰጥቶት ሊመረመር የሚገባው ይዘቱ እንደሆነ ‹‹ኦርቶዶክሳዊው ስነፅሁፍ›› የተባለው ጽሁፍ እንደሚከተለው ያብራራል፡፡

> ‹‹ ክርስቲያናዊ ግጥም የግጥም አይነቱን፣ ምጣኔውን፣ እንዲሁም ሌሎች ርእሶችን ግጥምን በተያያዘ እየዘረዘረ ሲያስተምር ዋናው አንድ መንፈሳዊ ጽሁፍ ፀሀፊ ፅሁፉን ምእመኑ በሚገባው መልኩ እንዲረዳው ያስችለው ዘንድ መመዘኛ እንዲሆነው ታስቦ ሲሆን ነገር ግን ኦርቶዶክሳዊ ግጥም ለቅርጽ ብቻ ሲባል የሚጻፍ እንዳልሆነ እና ፅሁፉ የያዘው መልእክት ከይዘት አንጻር አጽንኦት ተሰጥቶት ሊመረመር እንደሚገባ ጸሀፊው ግነዛቤ ሊኖረው ይገባል›› (ገጽ 14-15) ካለ በኋላ የጽሁፎቹ መመሪያ መስፈርቶችን እንደሚከተለው ይዘረዝራል፡፡

ሀ/ **እምነት** ፡- ቤተ ክርስትያን ከምታምነው ውጪ የራሱን አስተያየት ወይም ፍልስፍና መጨመር የለበትም፡፡ ከክርስቲያናዊ እምነት ውጪ የሆነ መልእክት አስተላልፎ አንባቢውን ወደ አልተፈለገ መንገድ መርቶ እንዳያደናግር እያንዳንዱን ግጥም ይዘት ለአባቶች እና ለታላላቅ ወንድሞች ሊያሳይ ይገባል፡፡

ለ/ **ስርአት**፡- ቤተክርስትያን የቅዳሴ፣ የጸሎት፣ የጥምቀት፣ የበአላት፣ የአጽዋማት … ወዘተ ስርአት አላት፡፡ ግጥማችንም ይህን ማፍለስ የለበትም፡፡

ሐ/ **ትውፊት**፡- ቤተ ክርስትያን ብዙ በትውፊት የተቀበለቻቸው ሀብቶች ባለቤት ናት፡፡ ከእነዚህም ለምሳሌ የስእል፣ የቤተ ክርስትያን አሰራርና አለባበስ ይጠቀሳሉ፡፡ ግጥማችንም እነዚህን ትውፊቶች የሚጠብቅ መሆን አለበት ይላል፡፡ በአጠቃላይ ጽሁፉ

የቤተ ክርስትያን ግጥም ይዘት የኃጢአትን ክፉነት ፣ የጽድቅን በጎነት፣ የኃጥአንን መመለስ፣ የፃድቃንን መፅናናት የሚያስተምር፣ የሰው ልጅ ድኅነት የሚያሳይ፣ የእግዚሐብሔርን ቸርነት፣ የቅዱሳንን አማላጅነት እሚመሰክር፣ የቤተክርስትያንን ትምህርት እሚገልጥና የቤተ ክርስትያንን ቅድስና የሚያሳይ መሆን እንዳለበት አጽንኦት ይሰጣል፡፡

በተጨማሪም ክርስቲያናዊ ግጥም ለማዝናናት ሳይሆን ለማስተማር ተብሎ መፃፍ እንዳለበት ይገልፃል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የግጥሞቹ ይዘት ትንተና

በ ‹‹ቬነስያ እና ሌሎች›› እና በ ‹‹ከሰይጣን ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅና ሌሎች›› በሚሉት መፅሀፎች ውስጥ 34 ግጥሞች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ጥናትም 34ቱም ግጥሞች ተንትነዋል፡፡

ግጥሞቹ ከሚያነሱት ርዕስ ጉዳይ አንጻር ታይተው በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፋፍለዋል፡፡ ይኸውም ለእግዚአብሔር የተገጠሙ፣ ለቅድስት ድንግል ማርያም የተገጠሙ፣ ለቅዱሳን መላእክት የተገጠሙ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ተአምር ስለተደረገላቸው ሰዎች የተገጠሙ፣ ለቅዱሳን አባቶች የተገጠሙ፣ እና ለልዩ ልዩ ጉዳዮች የተገጠሙ በሚል ሲሆን እያንዳንዱ ርእሰ ጉዳይ የምስጋና፣ የልመና፣ የንስሐ፣ የስብከት የነፍስና ስጋ ሙግት እና የእንቢተኝነት በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች ተካፋፍለዋል፡፡

ከቀረቡት ግጥሞች ውስጥ ለእግዚአብሔር የቀረቡት 8 ያህል ሲሆኑ ለቅድስት ድንግል ማርያም የቀረቡት ደግሞ አምስት ናቸው፡፡ ሌሎቹን በዝርዝር ስንመለከት! ለቅዱሳን መላእክት አንድ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ተአምር ስለተደረገላቸው ሰዎች ስድስት፣

ለቅዱሳን አባቶች ሁለት እና ስለልዩ ልዩ ጉዳዮች፣ አስራ ሁለት ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| የግጥሞቹ ይዘት | ብዛት | ለእግዚአብሔር | ለድንግል ማርያም | ለቅዱስ መላእክት | ለቅዱሳን አባቶች | በመጽሐፍ ቅዱስ ተአምር ስለተደረገላቸው ሰዎች | ስለልዩ ልዩ ጉዳዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምስጋና | 9 | 3 | 3 | - | 1 | 2 | - |
| ልመና | 4 | 2 | - | 1 | 1 | - | - |
| ስብከት | 15 | 2 | 2 | - | - | 2 | 9 |
| ንስሐ | 3 | 1 | - | - | - | 2 | - |
| እንቢተኝነት | 2 | - | - | - | - | - | 2 |
| የነፍስና የስጋ ሙግት | 1 | | | | | | 1 |
| ድምር | 34 | 8 | 5 | 1 | 2 | 6 | 12 |

ከላይ በሰንጠረዥ ለመግለፅ እንደተሞከረው የስብከት ግጥሞች ከፍተኛውን ቁጥር ይዘው ይገኛሉ ከዚያ በመቀጠል የምስጋና ግጥሞች ሁለተኛነት ደረጃን ይዞ ይገኛል ሌሎቹ የንስሐ፣ የልመና፣ የነፍስና ስጋ ሙግትና የእንቢተኝነት ግጥሞች አነስተኛ ቁጥር አላቸው፡፡

## 3.1 ለእግዚአብሔር የቀረቡ ግጥሞች

እግዚአብሄር የሚለው ቃል የግዕዝ ሲሆን የተተረጎመው ‹ኤል› ከሚለው የእብራይስጥ ቋንቋ ነው በአማርኛም ኃይል የሚል ትርጉም አለው፡፡ ኤልሻዳይ ማለት ደግሞ ሁሉን ቻይ ማለት ነው፡፡ በማለት አስራት ገ/ማርያም ‹‹ትምህርተ መለኮት›› በተሰኘው መጽሐፋቸው ያስረዳሉ (1991-8)፡፡ በመቀጠልም በዚሁ ገጽ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌሎች የእግዚአብሔር ስሞች እንደሚገኙ ይገልፃል፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ያህዌ እና አዶናይ ሲገኙ፤ ያህዌ ማለት ያለና የሚኖር ማለት ሲሆን አዶናይ ማለት ደግሞ ጌታ ማለት እንደሆነ ይገልፃል እግዚአብሔር የሚለው የግዕዝ ቃል ወደ አማርኛ ሲተረጎምም "የሀገር ወይም የዓለም ጌታ" የሚል ትርጉም እንዳለውም ያብራራል፡፡ ይህን እንደ መንደርደሪያነት ካነሣን ለእግዚአብሔር የቀረቡ ግጥሞችን ወደመተንተን እንግባ፡፡

### 3.1.1 የምሥጋና ግጥሞች

እግዚአብሔር ምሥጋና የባሕርዩ እንደሆነ፣ ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው አስቀድሞ ባህሪው ባህሪውን እያመሰገነ ይኖር እንደነበር እና ሰውና መላዕክትም የተፈጠሩበት ዋና አላማ ስሙን ለማወደስ ክብሩንም ለመውረስ እንደሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታስተምራለች። በነዚህ የግጥም መጻሕፍትም ሦስት ያህል የምስጋና ግጥሞች ለእግዚአብሄር ቀርበው እናያለን።

ያለ ትናንት ቀዳማዊ

ያለ ዛሬ ማዕከላዊ

ያለ ነገ ደኀራዊ (ከሰይጣን፣ 34)

ይህ ግጥም የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊነት ይገልፃል። እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረ አሁንም ያለ እና አለምን አሳልፎ የሚኖር ህያው ዘለዓለማዊ አምላክ እንደሆነ ያስረዳናል ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በራዕዩ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት እንዲህ በማለት ያስረግጥልናል። ‹‹ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሄር አምላክ ሁሉን የያዘ፣ የነበረና ያለ የሚኖርም›› (ራዕ 4÷8) በተጨማሪም አባ መልከጼዴቅ በትምህርተ ክርስትና መጽሐፋቸው የእግዚአብሄርን ዘለዓለማዊነት እንደሚከተለው ይገልፁታል፡- ‹‹በእግዚአብሄር ዘንድ ማርጀት፣ማፍጀት መለወጥ ከቶ የለበትም። ይኸ ሁሉ የፍጡር እንጂ የፈጣሪ ጠባይ አይደለምና›› (መልከጼዴቅ፣1984፣15)

ያለድካም የፈጠረ (ገጽ 34)

እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው የሚኖሩትን ጭምር ለመፍጠር የፈጀበት ጊዜ ስድስት ቀናት ናቸው ። እነዚህንም ከአዳም ውጪ በመናገር እና በማሰብ ብቻ እንዲሆኑ አደረገ እንጂ በድካም አይደለም። (እነ ስነታየሁ 8-9)

የማይሸሙት ንጉሥ

እሳት የማይዳሰስ (34)

‹‹እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው›› (መዝ 73÷12) እንዲል ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ ገጣሚውም እግዚአብሔር በሰው ሊሾም እንደማይቻል ይነግረናል፡፡ በተጨማሪም አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ‹‹እሳታውያን የሚሆኑ ሱራፌልና ኪሩቤል ሊነኩት የማይቻላቸው በእውነት እሳት ነው›› (ሕርያቆስ፣1993፣162) እንዳለው ሁሉ ግጥሙም ሊዳሰስ የማይቻል ፍጹም እሳት ነው በማለት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራል፡፡

የማያበድሩት ባለጸጋ

ሁሉን የማይዘነጋ

ከሀሌ ኩሉ አልፋና ኦሜጋ (34)

ግጥሙ እግዚአብሔር አምላክ ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ የሆነ፣ ያለፈውን የማይረሳ የሚመጣውን የሚያውቅ፣ ሁሉን ነገር ማድረግ የሚችል አምላክ መሆኑን ያስረዳል፡፡ እርሱ ብቻውን ለመሥራት ጀመረ፤ እርሱ ብቻውን ፈጸመ፣ ከቶ ደክሞት ሰልችቶት የተወው ነገር የለም፡፡ ረዳት የማይሻ አምላክ ነው፡፡›› (መልከጸዴቅ1984፣15)

ሌላው ግጥም ደግሞ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ጠባቂነት፣ ይቅርባይነት፣ ፍቅር እጅግ ብዙ መሆኑን ይገልፃል፡፡

ስምህን ሳልጠራ ከዋልኩበት

ከኔ ያልተለየህበት በምሕረት

በይቅርታህ የጠራኸኝ ባባትነት

ይበዛል (ከሰየጣን፣105)

ሳንጠይቅ የሚስፈልገንን አውቆ የሚሰጠን ከማናውቀው አደጋ የሚጠብቀን፣ ብንበድል በደላችንን ሳያስብ በፍቅር ወደ እርሱ የሚስበን የፍቅሩ ብዛት ወሰን የሌለው እንደሆነ ይነግረናል፡፡‹‹ሳንለምን የምንሻውን የሚሰጠን ፤ ሳንጠራጠር ለምንለምነውን የሚሰማን›› እንዲል መጽሐፈ ኪዳን ዘነግህ (ገጽ 11)

እንዲበዛልን መጥተሀል

እንዲበዛልን ሞተሀል፡፡ (ከሰይጣንጋር ፣105)

እግዚአብሔር አምላክ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ከድንግል ማርያም ሰው የሆነው፤ በኋላም አዳምን ከነልጆቹ ከሲኦል ለማውጣት ሲል መከራን ተቀብሎ ተሰቅሎ የሞተው ፍቅርነቱ አገብሮት መሆኑን ገጣሚው እንዲህ ሲል ያቀርበዋል፡፡

ከምድር አሸዋም ሆነ

ከሰማይ ከዋክብት ብዛት

ለመቁጠር የማልችለውን

የደግነትህን ብዛት

ራሴን በዚያ ውስጥ ሳየው

ማንነቴን ስመረምር

እኔ ማነኝ ምንም ነኝ

ከቁጥር የማልደመር

(ከሰይጣን ጋር ፤166)

ገጣሚው አምላኩ ያደረገለት ውለታ ከራሱ ጋር በማነፃፀር የአምላኩ ውለታ ብዛት ከራሱ ማንነት ጋር ሲነጻጸር የርሱ ማንነት ባዶ፣ ምንም እንደሆነ ይገልፃል፡፡

### 3.1.2 የልመና ግጥሞች

የሰው ልጅ ምንም ነገር በራሱ ማድረግ ስለማይችል የሚፈልገው ነገር ሁሉ እንዲፈጸምለት ሁሉን ቻይና ቸር ነው ወደሚለው አምላኩ እንዲሁም ምህረትን ያሰጡኛል ወደሚላቸውን ቅዱሳን ይለምናል ፤ ይማፀናል ገዛኸኝ ጌታቸው በሐመር መጽሄት ስለ ልመና የሚከተለውን ጽፏል ‹‹ለማኙ በትህትና ከተለማኙ ረድኤትና አማላጅነትን ይለምናል፡፡ ይህ ልመና ሁለት አይነት መልክ አለው አንዱ ሀጥያትን በመናዘዝ ስርየትንና ይቅርታን የሚጠይቅበት ሲሆን ሁለተኛው ግን በጠላት ላይ

በቀለምና አሸናፊነትን ለማግኘት የሚቀርብ ነው፡፡››(ሐመር፣31) ከነዚህ የግጥም መጻሕፍትም ሁለት ያህል ለእግዚአብሔር የቀረቡ የልመና ግጥሞች እናገኛለን እንደሚከተው ተተንትነዋል፡፡

ባይፈቅድ ብቃቴ

ቢጎድልም እምነቴ

እኔም እንደ አቅሜ አደግድጌ ቆሜ

በሰጠኸኝ ጸጋ ባብቴ ተጠቅሜ

ሳልርቅ ከመቅደስህ በእምነት ተተክዬ

እንዳመሰግንህ እርዳኝ ፈጣሪዬ

(ከሰይጣንጋር፣128)

ገጣሚው ምንም እንኳን ምግባረ ጎዶሎና እምነተ ቢስ ብሆንም ፍቅርህ በዝቶልኝ፣ በተመስጦ ሰማየ ሰማያት ተጉዤ፣ እንዳቅሜ በሰጠኸኝ ጸጋ በቤትህ ጸንቼ በእምነት እንዳመሰግንህ እርዳኝ በማለት ፈጣሪውን ይለምናል፡፡

ድንገት ብትነበኘኝ

ባዶ ቃርሚያ እንዳልሆን

ገጣሚው ምግባርን ከሀይማኖት አስተባብሬ ሳልይዝ፣ በንስሐ ከኃጢአቴ ሳልታጠብ በጌታ እንዳልነበኝ (እንዳልሞት) በማለት፤ በዚህ በሰዎች መሀከል ፍቅር በጠፋበት ዘመን እንዲያወጣው አምላኩን ይለምናል፡፡

ከቤቴ ሰው ሳጣ

እጅጉን ስሰጋ

ከዚህ መሀል አውጣኝ

አልፋና ኦሜጋ፡፡ (ከሰይጣን ጋር፣132)

### 3.1.3 የንስሐ ግጥሞች

‹‹ንስሐ ማለት “ነስሐ” ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን ፍቺውም ሐዘን፣ ፀፀት፣ቁጭት….. የኃጢአት ካሣ ማለት ነው፡፡ ሰው ከአምላኩ የሚለየውን ሥራ በሠራ ጊዜ ኀሊናው እረፍት ይነሣዋል፡፡ በዚህም መሠረት ክርስቲያን በበደለ ቁጥር ንስሐ በመግባት፣ ተፀፅቶ ይቅርታ መጠየቅ ይገባዋል፡፡›› (እሸቱ፣1999፣9)

በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የንስሐ ግጥሞች እንመልከት፡፡

ልኑር አልኩ እንደቃልህ

እንደፈቃድህ ላሳልፍኽ (sic)

ለበደሉህ መካስህን

ዓለሙ ሲሰቅልህ በግፍ

እኔም አንተኑ ልከተል

እንደሐሳብህ ልመላለስ

ስንት ጊዜ ሁሉን ልተው

የበደሉኝንስ ልካስ

ዐይኔ ሲለይ ከመስቀሉ

ጆሮዬ ሲርቅ ከቃሉ

እላለሁ ስንቴ በደለኝ

በቂም አረንቋ ስወድቅ

የበደልን ካባ ስለብስ

ሰባት ጊዜ ሰባ ይቅርብኝ

ቃል በእምነት ያልተዋሐደ

ቀራንዮን ብቻ አሳየኝ

ልቤ ይቅርታን በለመደ፡፡ (ከሰይጣን፣130)

ይህ ግጥም ‹‹ ስንት ጊዜ ይቅር ልበል›› የሚል ርእስ የሰጠችው ገጣሚዋ የጌታን ስነ-ስቅለት ባሰብኩ ጊዜ፣ ሲበድሉት እንዳልተበቀላቸው፤በአንጻሩ ሲሰቅሉት ‹‹የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው›› ብሎ ሲጸልይ፣ ጎኑን የወጋውን ሰው አይን ሲያበራ፤አዳም ቢበድለው ሲክሰው ይህን ሁሉ ሳስብ እኔም እንደፈቃድህ እኖራለሁ የበደሉኝን ይቅር እላለሁ እንደውም እክሳለሁ ብዬ ቃል ከገባሁ በኋላ ከቤተክርስቲያን ከወንጌል ትምህርት ስርቅ ደግሞ ቃሌን ዘንግቼ የሰው ኃጢአት እቆጥራለሁ፣እታበያለሁ እንኳን የበደሉኝን ልክስ ለበቀል እነሳሳለሁ፡፡ ቃሌ በተግባር አልተገለፀምና ጌታ ሆይ ልቤ ይቅርታን እንዲለምድ ያንተን ፍቅር ቀራንዮን በልቤ አትምልኝ፤ በማለት በፀፀት ትለምናለች፡፡

ሌላው ገጣሚ ደግሞ ‹‹ ዳግማዊቷ መግድላዊት ›› በሚል ግጥሙ በዓለም ኃጢአት ወድቆ ከእግዚአብሔር ቤት ርቆ ይኖር የነበረ ቢሆንም በኋላ ግን በበደሉ ተፀፅቶ ንስሐ እንደ ገባና ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል እንደበቃ፤ እግዚአብሔርም በሠራው ኃጢአት ሳይፀየፈው፤ በመመለሱ ተደስቶ እንደተቀበለው ይናዘዛል፡፡

በእንባዬ ጠበል ተጠበልኩ

በንስሐ ሕይወት ታጠብኩ

ለሥጋ ወደሙ ታደምኩ (ቬነስያ÷ 75)

### 3.1.4 **ስብከት**

‹‹ስብከት የሚለው ቃል ሰበከ ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን አስተማረ አዋጅ ነገር የሚል ትርጉም አለው፡፡›› በማለት ዲያቆን ደስታ ወርቁ ‹‹ አውደ ስብከት በተሰኘ መጽሐፉ ይገልፃል (ደስታ ፣1) በመቀጠልም ከዚህ መዝገበ ቃላዊ ትርጉም ባሻገር ፅንሰ ሀሳብን መሰረት በማድረግ ስብከትን የአምልኮት አንዱ ክፍል፣ ትእዛዘ እግዚአብሔር፣ ምስክርነት የምንሰጥበት፣ ድኅነት የሚገኝበት መንግስተ እግዚአብሔር የምትገለጥበት

በማለት የትንታኔ ትርጉመሞችን ሰጥቶታል (ደስታ፣1-3) በእነዚህ መጽሐፎችም የክርስቶስን ትንሣኤ የሚሰብክ ግጥም እናያለን፡፡

ሥጋን ተዋሕዶ

በፈቃዱ ቢሞት

እንዴት ይዘነጋል

የወልድ ጌትነት

ይህ ስንኝ አምላክ ከሰማያት ወርዶ ባሕርዩን ዝቅ አድርጎ ከድንግል ማርያም የሰውን ሥጋ ተዋህዶ በፈቃዱ ተወልዶ በፈቃዱ ቢሞት አምላክነቱን፣ጌትነቱን መዘንጋት የለብንም ይላል፡፡

በደረቅ ግንባር ላይ

ዓይንን የፈጠረ

የዮሐንስ ወንጌል ሲወለድ ጀምሮ የአይን ምልክት እንኳን የሌለውን ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደመሬት እንትፍ ብሎ በምራቁ ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን አይኖች በመቀባት እንዲያይ በማድረግ ተአምር መስራቱን ይገልፃል፡፡ (ዮሐ. 9÷14)

ከሳሹን ዲያብሎስ

በቃል ያሳፈረ

ሰይጣን በአይሁድ ላይ በማደር ኢየሱስ የሚሠራውን ሁሉ በመከታተል ይቃወመው ነበር፡፡ ኢየሱስም ከመነሻው አይሁድ በተንኮል እሱን የሚከሡበትን ነገር ለመፈለግ በመኼድ ጥያቄ ሲጠይቁት ሀሳባቸውን ቀድሞ ያውቅ ነበርና መልሶ እነሱኑ በመጠየቅ የሚናገሩትን ያሳጣቸው እንደነበር ገጣሚዋ ታነሳለች፡፡ (ዮሐ 8÷1-10) በተጨማሪም በማቲዎስ ወንጌል ም4 ÷ 1-11 እንደተጻፈው ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከፆመ በኂላ ዳያብሎስ ሊፈታተነው ቀርቦ ነበር፡፡ ኢየሱስ እንደተራበም አውቆ ‹‹ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እንዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል›› ሲለው ኢየሱስም ‹‹ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ

አይኖርም ተብሎ ተፅፎአል፡፡›› በማለት መልሶለታል ዳግመኛም ‹‹ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ ወደታች እራስህን ወርውር›› አለው፡፡ ኢየሱስም ‹‹ጌታ አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፏል›› በማለት መለሰለት በመጨረሻም የአለምን መንግስት ሁሉ ክብር አሳይቶት ‹‹ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሀለሁ›› ቢለው ያን ጊዜ ኢየሱስ ‹‹ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታ ለአምላክ ስገድ እሱን ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና›› በማለት መልሶለታል ፡፡ ከላይ እናዳየነው ዲያቢሎስ ከመፅሀፍ ጥቅስ እየጠቀሰ ቢፈታተነው እየሱስ ክርስቶስም ጥቅስ በመጥቀስ ዲያቢሎስን እንዳሳፈረው ገጣሚዋ ታነሳለች፡

የነ ሙሴ  አምላክ

የአልአዛር ትንሣኤ

በማለት ገጣሚዋ አልአዛር በሞተ በአራተኛ ቀኑ ከመቃብር እንዳስነሣው ትሰብካለች (ዮሐ 11÷43) ፡፡ በመጨረሻም ጌታ የአዳምን ሥጋ የተዋሐደበት ምሥጢር ያልገባቸው፣ አምላክነቱ ያልተገለፀላቸው ሥጋው ከመቃብር እንዳይሰረቅ ቢያስጠብቁም ጌታ ግን ያለማንም አጋዥነት ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቷል በማለት ገጣሚዋ ትንሣኤውን ትሰብካለች፡፡

የተዋሕዶን ምሥጢር

ፍጹም ያልተረዳው

መቃብሩን ከቦ

ታጥቆ ሲጠብቀው

ተነሥቷል ኢየሱስ

የአብ ቃል ሕያው ነው፡፡ (ቬነስያ፣ 211)

ሌላው ግጥም ደግሞ ‹‹የበለሷ ሚስጥር›› የሚል ሲሆን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 21÷19 ያለውን ታሪክ መሠረት በማድረግ እንዲህ ይለናል፡፡

አጠገቧ ደርሶ

በእጁ ቢዳብሳት

ከቅጠል በስተቀር

በለሷ ባዶ ናት፣ (ከሰይጣን ጋር÷ 86)

‹‹በመንገድ አጸበለስን አየ፤ ፍሬ ማገኝባት ብሎ ወደርሷ ሄደ፣ከቅጠል ብቻ በቀር ፍሬ አላገኘባትም እንግዲህ ወዲህ ፍሬ አይገኝብሽ ብሎ ረገማት ያንጊዜ ፈጥና ደረቀች፡፡›› የሚለውን የወንጌል ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ንባብና ትርጓሜ እንመሚከተለው ያብራራዋል፡፡ ‹‹ሰው በሆነ ጊዜ ፣ ሰው ሆኖ ሲያስተምር ከሰው ፍቅር ተራበ፣ እስራኤልን በኢየሩሳሌም አገኝ ሀይማኖት (ምግባር) ባገኝባቸው ብሎ ሄደ፤ አላገኘባቸውም እስራኤል ከመባል በቀር፡፡ ደግ ሰው አይገኝብሽ ብሎ ረገማት ያን ጊዜ ደግ ሰው ጠፋ›› (የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ንባብና ትርጓሜ ፣198)፡፡

ግጥሙም መንፈሳዊ ፍሬን ካላፈራን የጌታን ትዕዛዝ ካልፈፀምን በስተቀር በአለባበስና በአነጋገር ቤተክርስቲያን በመመላለስ ከሩቅ ለሚያየን እውነተኛ ክርስቲያን መምሰል ዋጋ የለውም የሚል መልዕክት አለው፡፡

### 3.2 ለድንግል ማርያም የቀረቡ ግጥሞች

ድንግል ማርያም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ዘንድ ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ የምትከበር ነች፡፡ ‹‹ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እመቤታችን በአምላክ ልቡና ታስባ ትኖር ነበር›› እንዲል መቅድመ ተአምረ ማርያም፡፡ (ገጽ 27) ድንግል ማርያም ለአዳም መዳን ምክንያት እንደሆነች በዚሁ መፅሀፍ ተፅፎ ይገኛል (ገጽ 29) በምዕመናኑም ዘንድ እጅግ ከፍ ያለ ከበሬታና ፍቅር አላት፡፡ በእነዚህ መጻሕፍትም ለድንግል ማርያም የተገጠሙ ግጥሞችን እናገኛለን፡፡

#### 3.2.1 ምስጋና

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለድንግል ማርያም ምስጋናን ማቅረብ መነሻው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈው የሚገኙት የቅዱስ ገብርኤል ‹‹ደስ ይበልሽ ጸጋን የሞላብሽ ሆይ! ጌታ ካንቺ ጋር ነው፡፡ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፡፡›› (ሉቃ 1÷28-29) የሚል ሰላምታና መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰዎች በብሉይ

ኪዳን በዐይነ ትንቢት በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በግልጥ እያዩዋት ያቀረቡላት ምስጋናዎች እንደሆነ ታስተምራለች፤ ሰሎሞን "ወዳጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ! ነውርም የለብሽም" (መኀልየ መኃልይ 4፣7 ) እንዳለ፤ ኤልሳቤጥም በታላቅ ድምጽ ጮኻ "ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ! የማሕጸንሽ ፍሬ የተባረከ ነው! የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?" እንዳለች (ሉቃ.1÷41-46) ፡፡

እንደቤተክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ፍጥረታት በተለይም ደግሞ የሰው ልጆች ድንግል ማርያምን ማመስገን አለባቸው- ድንግል ማርያም ራሷ ‹‹ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል›› (ሉቃ 1፣ 48-49) ብላለችና፡፡

በዚህም ምክንያት ይመስላል በነዚህ መጽሐፎች ውስጥ ለድንግል ማርያም የቀረቡ የምስጋና ግጥሞች አሉ፡፡

ለአባታችን ለሕርያቆስ ዕውቀት ሆነሽ

ለእኛ የሚተርፍ ጥበብ ገልፀሽ

ግጥሙ የሚተርክልን ቅዳሴ ማርምን ለደረሰው የቤተክርስቲያን አባት፤ ለአባ ህርያቆስ ድንግል ማርያም ስላደረገችለት ተዐምር ነው፡፡

ከአዋራጆች እጅ አዳንሽው

በፊታቸው አከበርሽው

ሞገስ ክብር አክሊል ሆንሽው

ዕውቀት ገልፀሽ አራቀቅሽው

(sic) ኅሣዕ ልብየ አሰኘሽው

እመቤቴ ብሎ ሲልሽ

ረዳሽው በታምርሽ (ቬነስያ፣46)

ይህ አባት በወቅቱ ዕውቀት ባይኖረውም ያንቺ ፍቅር የበዛለት ነበርና በምድር ትምህርታቸው የሚኩራሩ ቀሳውስት ሊሳለቁበት በፈለጉ ጊዜ የእመቤቴ ምስጋና

እንደባህር አሸዋ፣ እንደ ሰማይ ኮከብ በዝቶልኝ ፤ እንደምግብ ተመግቤው ፣ እንደመጠጥ ጠጥቼው እያለ ይመኝ ነበርና አንቺ ተገልጸሽለት በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ቅዳሴሽን እንዲቀድስ ረዳሽው፤‹‹ ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ እኔስ የማርያምን ምስጋና እናገራለሁ በማብዛት አይደለም በማሰነስ እንጂ›› ማለት ሲጀምር ሊሳለቁበት የፈለጉ እንዲደነቁ በታላቅ ክብርም እንዲያከብሩት አደረግሽ፡፡ በማለት ድንግል ማርያምን ያመሰግናል፡፡

የፆምን ልዩ ጣዕም

የምታስቀምሺ

የዲያብሎስን ጦር

ድል የምትነሺ

(ከሰይጣን ጋር÷74)

ገጣሚዋ ብዙዎቹ የቤተክርስቲያኒቷ አማኞች ፆምን የሚጀምሩት በህፃንነታቸው ለአሥራ ስድስት ቀናት ብቻ በምትጾመው በፍልሰታ ጾም በመሆኑ የጾም ጣዕም የሚታወቅብሽ አንቺ ነሽ በማለት ድንግል ማርያምን ታመሰግናለች፡፡ በተጨማሪም ዲያብሎስን ድል ማድረግ የሚቻለው በጾም ነውና እኛም የፍልሰታ ጾምን ስንጾም ባንቺ ዲያብሎስን ድል ይመታል ትላለች፡፡

በዚህ ግጥም ደግሞ ገጣሚዋ ድንግል ማርያምን በቤተልሄም በመመሰል እንደሚከተለው ታመሰግናታለች፡፡

የሴም በረከቱ

ማዕከለ ምድር

ኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰከረ፤ እርቃኑንም ተኝቶ ሳለ ከነአን የተባለው ልጁ አይቶ ለወንድሞቹ ለሴም እና ለያፌት ቢነግራቸው እነሱ ያባታቸውን እርቃን እንዳያዩ ወደኋላ ሄደው ልብሳቸውን ጋርደውታል፡፡ ኖህም ከስካር ከነቃ በኋላ እግዚአብሔር በሴም ድንኳን ይደር በማለት ሴምን መርቆታል፡፡ የሴም ድንኳን

የተባለችው ለጊዜው የአብራሀም ድንኳን ብትሆንም ፍጻሜዋ ግን ድንግል ማርያም ናት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በማህጸኗ አድሯልና፡፡ (ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ፣ 81-82)

መሶበ ወርቅ የሆንሽ

ለሰማይ ኅብስት

ቅዱስ ኤፍሬም በእሁድ ውዳሴው ድንግል ማርያምን ‹‹መና ያለብሽ የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ›› (ውዳሴ ማርያም) ይላታል ይኸውም ምሳሌው መሶበ ወርቅ የመቤታችን ፤ መና ደግሞ የጌታችን ነው በማለት የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ያስረዳል (ገጽ 195)

የብርሃን መሰላል

የተዘረጋብሽ

ከነሠራዊቱ

ንጉሥ ያረፈብሽ

ቅዱስ ኤፍሬም በማክሰኞ ውዳሴ ማርያም ድንግል ማርያምን ‹‹ ከምድር እስከ ሰማይ ተተክላ መላእክት ሲወጡበት እና ሲወርዱባት ያእቆብ በፍኖተ ሎዛ ያያት የወርቅ መሰላል አንቺ ነሽ›› ይላታል ( ገጽ )የውዳሴ ማርያም ትርጉምም ‹‹ የብርሀን መሰላል የእመቤታችን፣ ዙፋን የማህፀንዋ፣ ንጉስ የጌታ ምሳሌ ነው ፡፡››በማለት ይገልፃል፡፡

ከአርያም ዙፋን

ከአባቱ ሳይለይ

ረቂቅ መለኮት

ሥጋ ለብሶ ሲታይ

ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋን ተዋሀዶ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት በሰማይ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንደነበረ ሁሉ ከተወለደ በኋላም በሰማይ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አልተለየም ትለናለች፡፡

ቤተልሄም ሆነች

የዕርቅ አደባባይ (ቬነስያ፣ 122)

ሰውና አምላክ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ተጣልተው ሲኖሩ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ለብሶ ከድንግል ማርያም ሲወለድ መታረቃቸውን ግጥሙ ይናገራል፡፡

### 3.2.2. የስብከት

በእነዚህ ሁለት መጻሕፍት ውስጥ ሁለት ያህል ስለድንግል ማርያም ክብርና አማላጅነት የሚሰብኩ ግጥሞች ይገኛሉ፡፡

ነፍስ ከውስጥ ስትተክዝ

በሞት ሰቀቀን ተውጣ

መሸሸጊያ ሲፈለግ

የሚገባበት ሲታጣ

በሩ ተዘግቶ ከእልፍኙ

ወደ ስደት ስትጓዙ

ለክፉ ቀን መሸሸጊያ

እናትና ልጁን ያዙ፡፡ (ቬነስያ፤ ገፅ 28÷እናትና ልጁን ያዙ)

ከገባችሁበት ማጥ መውጣት ሲያቅታችሁ፣ ሐዘን፣ችግር፣ከባድ ፈተና ሲጋጥማችሁ ድንግል ማርያምን ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ጥሯት ይለናል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ድንግል ማርያምና ኢየሱስ ክርስቶስ ተለያይተው አያውቁም፤ከጽንሰት እስከ ከቤተልሔም፣ ከቤተልሔምም እስከ ቀራንዮ አብረው ነበሩ፡፡ አሁንም እናቱ በልጇ ክብር ተከብባ በሰማያዊ ዙፋኑ አብረው አሉ፡፡ (ያዕቆብ፣ 1994፣26) ፡፡

በተጨማሪም የሰው ልጅ በኃጢአት በወደቀ ጊዜ ፣ ግራ ሲገባው፣ በሰው መመካቱን ትቶ እናትና ልጁን ይያዝ በሰው መመካት ዋጋ የለውም፤ ዘለቂ መፍትሔ አያገኝም፤ ይልቁንስ ከአስፈሪው ከሁለተኛው ሞት ለመዳን፤ እናትና ልጁን ይማፀን ይላል፡፡ የሚቀጥለው ግጥም ርእሱ "ፊደል ሰው ገደለ" ይላል፡፡ ጉዳዩም የቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤትና ከእርሱ ጋር ተያይዞ የሚነሣው የድንግል ማርያም አማላጅነት ነው፡፡

"እናትና ልጅ ተጣሉ

ካንቺ ምን አለኝ ስላላት

የምልጃ ነገር አቆመ

ማርያም ከተአምሩ ምን አላት"

ተባለ አስባለ

እነ አያውቁን አስሞኘ

ፊደል ተገልብጦ

በሞት ተሰናኘ

ይህ ግጥም በሉቃስ ወንጌል (2÷1-12) ያለውን በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት የተደረገው የኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ተአምር በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞችና በሌሎች የቅዱሳንን አማላጅነት በማይቀበሉ የክርስትና ፈርጆች መካከል ያለውን የትርጉም ልዩነት መሠረት ያደርጋል፡፡ ግጥሙ በዚህ የቃና ዘገሊላ ተአምር የድንግል ማርያም አስተዋêያ የለበትም ማለት ወደ ሁለተኛው ሞት የሚወስድ የአላዋቂነት ትርጓሜ ውጤት የሆነ ስሕተት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ በመቀጠልም ንባቡ እንዲህ ሊተረጎም ይገባል በማለት የቤተክርስቲያኗን አስተምህሮ ተተግኖ እንደሚከተለው ያስቀምጣል፡፡

ዳሩ እናትና ልጅ ተግባብተው

ልመናዋ እንዳይቀር ሳይደረግ

በ ‹‹የሚላችሁን አድርጉ››

ከውርሬት ዳነ ባለሥርግ፡፡

ድንግል ማርያም ልጇን ‹‹የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም›› በማለት ስትነግረው ጌታ‹‹አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ፣ አላት›› የሚለውን አነጋገር ጠቅሶ “የእናቱን ልመና ንቆ ተወው፤ አልተቀበላትም” ማለት ተገቢ አለመሆኑንና ከጌታ እንዲህ ያለ አስተሳሰብ መጠበቅ “አባትና እናትህን አክብር!” ብሎ በሙሴ አማካይነት ትእዛዝ የሰጠውን የእግዚአብሔርን ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን “የራሱን ትእዛዝ ይጥሳል፡፡” ያሰኘዋል፡፡ ይህ ደግሞ “ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አይደለም፡፡” ወደሚል አጠቃላይ የክርስትና መሠረት የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት የሚንድ ድምዳሜ ላይ ያደርሳ፡፡ በማለት መምህር ኃይለማርያም ላቀው በመካኒሳ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የአውደምህረት ትምህርታቸው ጠቅሰዋል፡፡

ግጥሙ ከዚህ “የሞት” መንገድ ለማምለጥም የሚከተለውን የቤተክርስቲያኒቱን አስተምህሮ የተከተለውን ትርጓሜ መከተል ግድ እንደሚል ይሰብካል፡፡ እንደተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ ይህ ‹‹ከአንቺ ጋር ምን አለኝ›› የሚለው አነጋገር የእስራኤላውያን የክብር ንግግር ነው፡፡ ‹‹ያልሽውን እንዳልፈጽም ካንቺ ጋር ምን ጠብ አለኝ›› ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ድንግል ማርያም ቀጥታ ሄዳ ለአገልጋዮቹ ‹‹ልጄ የሚላችሁን አድርጉ›› ብላቸዋለች በምልልሳቸው ባይግባቡ ኖሮ አፍራ ዝም ብላ ትተው ነበር እንጂ ልጇ የሚሠራውን ተአምር አውቃ ይህን ትእዛዝ አታስተላልፍም ነበር፡፡ አገልጋዮቹም እርሷ እንዳዘዘቻቸው ልጇ ያለውን ሁሉ አደረጉ፤ በባዶዎቹ ስድስት ጋኖች ውኃ ሞሉ ውኃውም በፊት ከነበረው የወይን ጠጅ የበለጠ ጣዕም ወዳለው ወይን ጠጅነት በኢየሱስ ክርስቶስ ተቀየረ ይህ የሚያሳየው የድንግል ማርያም ምልጃ መሰማቱን ነው፡፡(እሸቱ፣122) ግጥሙ እንደሚከተለው ይቋጫል፡-

የወይን ጠጅ ተቀድቶ

ጋኑ ሁሉ ሞልቶ

እድምተኞው ሁሉ ረካ

እናትና ልጁ ተግባብተዋል ለካ (ከሰይጣን ጋር፣ 81)

### 3.3 ለቅዱሳን መላእክት የቀረቡ ግጥሞች

3.3.1. **ልመና**

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቅዱሳን መላእክት ሰውን በአማላጅነታቸው፣ በተራዳኢነታቸው ያገለግላሉ፡፡ ከፈጣሪ አማልደው ምሕረት ያሰጣሉ፡፡ ከፈጣሪ ምሕረትን ይዘው እንደሚመጡ ሁሉ የሰው ልጆችንም ልመና ወደ እግዚአብሄር ይዘው ይወጣሉ (ብርሀኑ፣1986 ገፅ 63) ፡፡ ቬነስያና ሌሎች በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አንድ ግጥምም ገጣሚው ለመላእኩ ልመና ያቀርባል፡፡

‹‹አንተ ውኃ መጠመቂያው››

አንተ መልአክ ፈጥኖ ሰሚው

እባክህን ተነቃነቅ

ሰው የለኝም የእኔን የሚያውቅ

ሰው የለኝም ሰው የምለው

ሰው የለኝም የኔ የምለው

ሽባነቴን ፈውስና

“እኔን› ስጠኝ የኔ ይሁን እንደገና፡፡

(ቬነስያ፣ 209)

ፈጥኖ ሰሚው መልአክ ሆይ መሻቴን የሚያደርግልኝ ሰው የለኝምና አንተ ተራዳኝ፣ ከበሽታዬም ፈውሰኝ በማለት ይማፀናል፡፡

በዮሀንስ ወንጌል 5፣2-4 እንደተጠቀሰው በኢየሩሳሌም በበጎች በር አጠገብ በእብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች በዚያም ብዙ በሽተኞች እና እውሮች አንካሶችም ሰውነታቸው የሰላ ህዝብ ነበሩ፡፡ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ ውሀውን ሲያናውጥ ቀድሞ ገብቶ ለመፈወስ የሚጠባበቁ፡፡ መልአኩ ውሀውን ለመቀደስ መስዋእትን ለማሳረግ ይወርዳል ፤ውሃውም የመለአኩን መውረድ ለማሳወቅ ፣ ለፈውስ ይናጣል በየጊዜው

አንዳንድ ድውይ ይፈውሳል ታምራት መደረግ እንዳልቀረ ለማሳየት መፈወሱ አይቀርም፤ በኦሪት ፍፁም ድኅነት እንዳልተደረገ ለማሳወቅ ከአንድ ሰው ውጪ ሌላውን አያድንም፡፡ እንዲል ትርጓሜ ወንጌል (ገጽ 477-478) ፡፡

### 3.4 ለቅዱሳን አባቶች የቀረቡ ግጥሞች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን "እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፡፡ ማንም ከነዚህ ከታናናሾቹ ለአንድ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኂለሁ ዋጋው አይጠፋበትም፡፡" (ማቴ፣10÷40-42) ለሚለው የወንጌል ቃል የምትሰጠውን ትርጓሜ መሠረት በማድረግ ለቅዱሳን፣ ለጻድቃን ለሰማዕታት ከፍ ያለ ክብር ትሰጣለች ከፈጣሪም እንደሚያማልዱ አጥብቃ ታስተምራለች፡፡

#### 3.4.1 ምስጋና

‹‹ማህሌተ ጽጌን የደረሰው በ14ኛው መ.ክ ዘመን የተነሳው አባ ጽጌ ድንግል ነው፡፡ ማህሌተ ጽጌ ግጥማዊ አካሔድ ያለው ድንቅ ኢትዮጵያዊ ድርሰት ነው፡፡ ይህ ድርሰት በማንኛውም ጊዜ የሚጸለይ ቢሆንም በተለየ ሁኔታ በቤተክርስትያን አገልግሎት የሚውለው ከመስከረም 26 እስከ ሕዳር 6 ባለው የመቤታችን የቅድርስት ድንግል ማርያም የስደት ዘመን ነው፡፡ በዚህ ወቅት በየሳምንቱ እሁድ ሌሊት በሙሉ የመቤታችንን ከልጇ ጋር ወደ ግብጽ መሰደድ እና መንከራተት እያደቡ የሚደረስ የምስጋና ጸሎት ነው፡፡››(ሐመር ነሀሴ/መስከረም 1993፣10) ገጣሚዋም እኝህን የቤተክርስቲያን አባት እንደምን ያለ እፁብ ድንቅ ጥበብ ተገልጸልህ ይህን የመሰለ ድርሰት ደረስክ እያለች ውዳሴ ታቀርብለታለች፡-

ምን አይነት ጥበብ ነው

ላንተ የተገለጸው

ላፍታ እማይቋረጥ

የገነት ጅረት ነው

ፍጥረት ተጎንጭቶ

ጠጥቶ የማይጠግበው፡፡ (ቬነስያ፣ ገፅ 80)

### 3.4.2 ልመና

በዚህ ግጥም ደግሞ ገጣሚዋ ቅዱሳን ሐዋርያትን ጴጥሮስንና ዮሐንስን አምላክ ከሰጣችሁ በረከት ተዘከሩኝ በማለት እደሚከተለው ትለምናቸዋለች፡፡

ፍቅርና ደስታ

ሰላምና ትዕግስት

እምነት የዋሕነት

ቸርነት በጎነት

ጥቂት ተዘከሩኝ

ባዶዬን ልሙላበት፡፡

(ከሰይጣን፣ 36)

### 3.5. በመጽሐፍ ቅዱስ ተአምራት ስለተደረገላቸው ሰዎች የተገጠመ

በወንጌል እንደሰፈረው ኢየሱስ ክርስቶስ 33 ዓመት ከስድስት ወር በምድር ላይ ሲመላለስ ብዙ ተአምራትን አድርጓል፡፡ በተለይ በዘመኑ የነበሩ ድውያንን ሲፈውስ፣ለምፃሞችን ሲያነጻ፣ዕውራንን ሲያበራ፣ሙታንን ሲያሥነሳና ሌሎች እፁብ ድንቅ ተአምራትን ሲያደርግ ነበር፡፡ በእነዚህ ሁለት መጽሐፎችም በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ተአምራት የተደረገላቸው ሰዎች በግጥም መልክ ታሪካቸው ቀርቧል፡፡እነዚህም ከብሉይ ኪዳን አጋር፤ከሀዲስ ኪዳን ደግሞ የአምንዝራይቱ ሴት፣ በቤተመቅደስ የምታገለግለው ርኩስ መንፈስ ያነበጣት ሴት፣ አስራሁለት አመት ሙሉ ደም ይፈሳት የነበረች ሴት እና እውር ሆኖ የተወለደው ሰው ተጠቅሰዋል፡፡

### 3.5.1. ምስጋና

በኦሪት ዘፍጥረት (16÷1--16) የአብርሃምና የሣራ ገረድ የሆነችው በኋላም ሣራ ለባሏ ለአብረሃም ሚስት ትሆነው ዘንድ የሰጠችው የአጋር ታሪክ ይገኛል፡፡ አጋር እመቤቷ ሣራ ፊት ብትነሣት፤ እስማኤልን እንደፀነሰች ኮበለለች በበረሀም ብቻዋን ብዙ ተሰቃየች፡፡ ከዚያም የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምታ መጽናናቷንና ሰው ክፉ ቢያደርግባት እንኳን እግዚአብሔር እንዳልረሳት "የሚያየኝን አየሁት" በማለት ምስጋና ታቀርብለታለች ይህንንም ገጣሚዋ እንደሚከተለው አቅርባዋለች፡፡

አጋር አለኝ ስሜን ጠርቶ

የልቅሶዬን ድምፅ ሰምቶ

ከላይ ሆኖ ቁልቁል እኔን ሲመለከት

ቀና ብዬ እኔም ያየኝን አየሁት

ቸር አባቴ እንዳልረሳኝ ተረዳሁት፡፡

(ቬነስያ፣121)

ከአስርቱ ትእዛዛት አንዱ የሆነውን "አታመንዝር" የሚለውን የሙሴን ሕግ ስትሽር የተያዘችው ሴት አይሁድ ተወግራ ትሞት ዘንድ እንዲፈርድባት ወደ ኢየሱስ በወሰዷት ጊዜ እርሱ በፍርድ ፈንታ በፍቅር እንድትሄድ ዳግመኛ ግን እንዳትበድል እንዳዘዛት ገጣሚዋ እንደሚከተለው ትገልፃለች፡፡(ዮሀ. 8፣1-11)

በደሌን ሲሰማ

ቸሩ የኔ ጌታ

በጣም አዘነልኝ

በመቆጣት ፈንታ

‹‹የጠፋሽው ልጄ

ዛሬ አገኘሁሽ

እንዳትበድይ

ለወደፊት ደግመሽ

እኔ አልፈርድብሽም››

ብሎ አሰናበተኝ

አባታዊ ፍቅሩን

በልቤ ሳለብኝ፡፡ (ከሰይጣን ጋር፣ 37)

3.5.2. **ንስሐ**

ገጣሚዋ በሉቃስ ወንጌል (8÷45) ላይ የምትገኘውን የኢየሱስን ቀሚስ ዳስሳ ተፈወሰች ሴት እምነት ጥንካሬ እያደነቀች ያንቺን ጥንካሬ፣ እኔ በስም ክርስቲያን ብሆንም ምግባረ ጎዶሎ ነኝና ያንቺን እምነት አስተምሪኝ በማለት ስለራሷ እየተፀፀተች ትማፀናለች፡፡

በኃጢያት ደምና በበደል የራስኩኝ

ስሙን ተሸክሜ ላልተጠቀምኩበት

ለኔም አስተምሪኝ ጌታዬን ልዳሰው

ሰባራውን ልቤን በዕምነት ልመልሰው፡፡ (ከሰይጣን ጋር፣ 12)

**3.5.3. ስብከት**

አስራ ስምንት አመት ሙሉ እርኩስ መንፈስ ያጎበጣትን አንዲት የቤተ መቅደስ አገልጋይ ጽናት እና በኋላም በጌታ መፈወስ ገጣሚዋ እንደሚከተለው ትሰብካለች (ሉቃ 13÷10-13)

በመጉበጥሽ ሳታኮርፊ

ጸጋ ብለሽ

በተመስገን ተቀብለሽ

ዓይንሽ ከሰው ላይ ተነቅሎ

ጌታን አይቶ ጌታን ብሎ

እሱው መጥቶ ሊጎበኝሽ

በቃሽ ብሎ እስኪምርሽ

ቤተ መቅደስ ውስጥ ተገኝሽ (ቬነስያ፣ 41)

ባጠቃላይም ምንም አይነት ችግር ቢደርስብን "አሜን" ብለን በአኮቴት ተቀብለን የእግዚአብሔርን የማዳን ቀን በቤቱ ሆነን መጠበቅ ነው እንጂ ማማረር አይገባም የሚል አንድምታ አለው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በወንጌል በጌታ ዐይኑ የበራለትን ሰው በመጥቀስ የትኛው አይንህ በራልህ መንፈሳዊው ነው ወይስ ሥጋዊው፤ የጌታን ክብር አሳየህ ወይስ ያንተ ውበት? እያለች ትጠይቃለች፡፡

ንገረኝ ምን ይታይሀል

እውን አይንህ በርቶልሀል?

የጌታ ክብር ግነቱ

የክንሩ ፀዳል ውበቱ

ቀራንዮ ጎልጎታ

የዋለበት ያለም ጌታ

… .

ጉብዝናህ አዋቂነትህ

የሚታይህ ከሆነ ሥጋህ

ካልረሳኸው አንተነትክን

አታይም በቃ እውር ነህ

አለማየት ነው ኃጢአት

ጌታን ከማሰብ ይልቅ ስለራሳችን የምንጨነቅ ከሆነ ከንቱ ነን ንስሐ ገብተን የአምላክን እፁብ ድንቅ የሆነ ተአምር ቸርነት ፍቅር ማሰብ ይገባናል ማለት እንደሚከተለው ታስተምራለች፡፡

እንዲያልህ አይንህ በደንብ

በሰሊሆም ውሀ ታጠብ

አንተን ሳይሆን ጌታህን

እየው እስኪ አምላክህን፡፡ (ቬነስያ ገፅ 74 ምን ይታይሀል)

**3.6 ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች የተገጠመ**

**3.6.1.ስለ ነፍስና ስጋ ሙግት የተገጠመ**

ጊዜያችን ካለፈ እንዳይቆጨን ኋላ

እንዝፈን አንዝፈን፣ እንጹም እንብላ፣
እንስጥ እንቀማ እየተባባሉ፣

ነፍስና ሥጋዬ በፈቃድ ተጣሉ፡፡

የሰው ልጅ ነፍስና ስጋ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ሲሚገቱ ይኖራሉ በፍፁም በፈቃድ አይስማሙም፡፡ የሥጋ ፈቃድ ምድራዊ ነው፡፡ መብላት ፣መዝፍን፣ መቀማት ፤ የነፍስ ፈቃድ ሰማያዊ ነው ከኃጢአት መቆጠብን ይመርጣል፡፡ ስለዚህ ፍጹም ተቃራኒ ናቸው፡፡ ገጣሚዋ ሥጋዬ ኃጢአት እንሥራ ! ነፍሴ ደግሞ ተው ለሁለታችንም አይጠቅምም እየተባባሉ ይጣላሉ ፤

በሐዘን በለቅሶ ራሱ ፈረሰ፣

አመድ ነሰነሰ በአፈር ተለወሰ

እንዲያ ሲደነፋ ሲዘል የነበረ

ከመድረኩ መሐል ሥጋ ወድቆ ቀረ (ከሰይጣን ጋር፣ 150)

ሥጋም ምን ያህል ጠንካራ ቢመስል፣ ቢኮፈስ ከነፍስ ከተለየ ምንም ዋጋ የሌለውም በስባሽ ነው ትለናለች፡፡

**3.6.2 የስብከት ግጥሞች**

‹‹ሁለቴ ተዳሰስ›› የሚለው ይህ ግጥም ደግሞ በአንድ ጊዜ ትምህርት አውቀናል በቅተናል ብሎ መኮፈስ ወደ ክሕደት ይወስዳል የሚል መልዕክት አለው፡፡

የዕውቀት ዓይንህ ሲበራ

መዳሰስ ልመድ አንዳንዴ

ተቀመጥ ካባቶችህ ሥር

ብቃት አይገኝም ባንዴ

ድጋሜ ተዳሰስ መጥተህ

ዓይኖችህ አጥርተው ይዩ

ተለማኝን ከለማኙ

ዛፍን ከሰው እንዲለዩ (ቬነስያ፣ 251)

ዘወትር ከአባቶች ዘንድ እየሄዱ መማር ተገቢ ነው አለዚያ ይደበላለቅብናል፡፡ የአምላክን ማንነት ከሰው ምንነት ለይተን ማወቅ አለብን፡፡ አባቶችን ደጋግመን በመጠየቅ የፈጣሪንና የፍጡርን ግንኙነት አጥርተን ለማወቅ  በቅን ልቦና እንማር በማለት ይሰብካል፡፡

‹‹ኩራትና ትዕቢት

የሞሉት አናት

ሰይፍና ጎራዴ

የመቱት አንገት

አይገላገሉም

እንዲህ በቀላሉ

ከመሬት ላይ ወድቀው

ሳይንከባለሉ። ›› (ቬነስያ፣ 8)

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ኩራትና ትዕቢት የዲያብሎስ መገለጫዎች ናቸው፤ በትዕቢቱ ከክብሩ ተዋርዷልና። እንዲሁም ትዕቢትና ኩራት የተሞላ ሰው አወዳደቁ አያምርም። በሰይፍ እንደተመታ አንገት በድኑ ከመሬት ይንከባለላል (ከሁሉ ያነሰ ይሆናል) የሚለን ‹‹ኩራትና ትዕቢት›› የሚል ርዕስ ያለው ግጥም ነው።

ባይኖር ኖሮ ተስፋ

የሚያጣፍጥ ኑሮን

ምድር ትሆን ነበር

የህያው አስከሬን

የሙታንም መንደር (ቬነስያ፣ 17)

ይህ ‹‹ባይኖር ኖሮ ተስፋ›› የሚለው ግጥም ደግሞ ፤የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር ችግር በደረሰበት ጊዜ፣ ሐዘን ሲጸናበት፣ ኑሮው የጨለመ ሲመስለው ነገን በብሩህ ተስፋ ባይጠብቃት ኖሮ ምድር ተስፋ በቆረጡ ፍጡራን ትሞላ፣ ህይወትም አይታይባትም ነበር በማለት ተስፋ ለሰው ልጅ ያለውን ጥቅም ይገልፃል።

“ልበ መንታ” የሚሰኘው ሚከተለው ግጥም ደግሞ ትኩረቱ

ሲቀደስ አስቀዳሽ

ሲዘፈን አቀንቃኝ

በከንቱ የሚሮጥ

ጊዜውን አባካኝ

…

ስደተኛ ሆኖ

ከሁለቱም ሀገር

ሁለት ያጣ ሆኖ

በከንቱ እንዳይቀር

ቅዳሴ መንፈሳዊ ተግባር ነው ዘፈን ደግሞ ኃጢአት ነው ሁለቱንም በአንድ ማስኬድ አይቻልም፡፡ ይህን የሚደርግ ሰው ጊዜውን በከንቱ ያሳልፋል፡፡ ፍጹም መንፈሳዊ ሆኖ በፍጹም ልብ አምላኩን አገልግሎ ከእዚህ ዓለም ሲያልፍ ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እንደ አባቶች በእምነት ጸንቶ ይኑር ይለናል፡፡

አስከትሎም የሰው ልጅ የዚህ ዓለም ኑሮው የስደት ነው እንጂ ዘለዓለማዊ አይደለም፡፡ ዘለዓለማዊ ቤቱ ከሞት በኋላ እንደ ሥራው የሚያገኛት ስፍራ ናት፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ የዚህ ዓለም ስደተኛ እንደሆነ ሁሉ የዚያኛው ዓለምም ስደተኛ እንዳይሆን ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲህ ሲል ይመክራል፡-

ልበ መንታነቱ

ይወገድ በዕምነት

ጽናትን ይታጠቅ

እንደ አበው ቀደምት (ቬነስያ፣ 97)

ሌላው ግጥም ደግሞ መኖር ማለት የሥጋን ፈቃድ ማሸነፍ በኃጢኣት ሲወድቁ በንስሐ በመመለስ ፣ በሐዘን ልብህ ሲሰበር በተስፋ በመጠገን፣የመከራ ማዕበል ሲያይል በእምነት በመጽናት፣ መከራን በመታገስ ነው ሲል እንዲህ ይሰብካል፡፡

ትእዛዙን ሰምተህ

ቃሉን እያወከው

መቼ ታገልክና

## ሥጋን አሸነፍከው

አለበለዚያ ኑሮህ ኑሮ አይደለም ልማዳዊ ጉዞ ነው ይለናል፡፡

ዓላማ ሳይኖርህ

በልማድ ተጉዘህ

መኖርን ሳትኖር

ለምን ትሞታለህ (ከሰይጣን ጋር፣ 114)

አዲስ ሰው ሳትሆን -ጽድቅን ሳታፈራ

አሮጌውን ሳትጥል -አዲስ መደረቱ

የዘመን ቅበላ - ይቅር ምናባቱ (ቬነስያ፣ 27)

ዘመን በተለወጠ ቁጥር ሕይወታችን ሳይለወጥ፣ ከኃጢኣት ሳንርቅ፣ ንስሐ ሳንገባ፣ አዲስ ዘመን በመጣ ቁጥር ከነኃጢኣታችን ቆይተን እኛ ሳንለወጥ ዘመን ተለወጠ ብሎ አዲስ ዘመን መቀበል ዋጋ የለውምና ከዘመኑ ጋር አብሮ በጽድቅ መለወጥን እናስብበት የሚል መልእክት ያለው ግጥም ደግሞ ‹‹ቅበላ›› የሚለው ነው፡፡

ገና መጣ ገና ሄደ

በዓል ከሆነ ኑሯችን

የይሁዳን ኮረብታ እረኞች

መቼ ይሆን መምሰላችን፡፡ (ቬነስያ፣ 160)

ጌታ በተወለደ ጊዜ በሌሊት ከብቶቻቸውን ይጠብቁ የነበሩ እረኞች የጌታን ልደት ሲሰሙ ወዲያው ወደ ቤተልሄም በመሄድ ሰግደዋል፡፡ እኛ ግን በገና ሰበብ የሥጋ ፍላጎታችንን እያሟላን ነው፡፡ ልባችንን ሰብረን ንስሐ የምንገባው ወደ እግዚአብሔር ዕቅፍ ገብተን ፍቅሩን የምናስበው መቼ ነው› ኧረ እንንቃ፤ በማለት ይመክራል፡፡

ሌላኛው ዕድሜህ ስንት ነው› የተሰኘ ግጥም ደግሞ ሲጀምር ዕድሜን ጠይቆ ነው፡፡ እንዲህ ይነበባል፡-

ስንት ዓመት አለፈህ

ጌታህን ካወቅኸው?

ተመችትኸዋል

ወይስ ቆረቆርኸው?

በስም ክርስቲያን ተብሎ በልማድ መመላለስ ጥቅም የለውም ራስህን መርምር፤የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈጸምክ ነው ወይስ በኃጢኣት ወድቀሀል፡፡

(sic) አሊያም ከደፈርክ

አደግሁኝ ለማለት

ስንት ዓመት ኖረሀል

ምንስ ሠራህበት? (ቬነስያ፣ 79)

ከምግባር የተለየ እምነት ጥቅም የለውምና እድገትህ የሚታወቀው፣ዕምነትህን በተግባር ስትገልፀው ነውና “አደግሁ፡፡” ብለህ ከተመካህ “ምን ሠራህ›” ሲል ይጠይቃል፡፡

ቀጥሎ የምንመለከተው ‹‹መክሊት ነው›› የሚል ርእስ የተሰጠው ግጥም ደግሞ ምንም እንኳን እስከ ዛሬ ምግባር ባይኖረን አሁንም ጊዜ አለንና በጊዜያችን እንጠቀም ይለናል፡፡

ዛሬ እድንነቃ

ተኝተን የነበርን

እንድንሠራበት

ስለሰጠን ዘመን

የነገን ነገር አናውቅም የኛ ቀን ዛሬ ነው እስከዛሬ በኃጢአት ያሳለፍነው ዘመን ይብቃን ወደ ንስሐ እንመለስ፡-

ፍሬ ላላፈራን

ወቅቱ ያዝመራነው

ጊዜ ላወቀበት

ማትረፊያ መክሊት ነው፡፡ (ከሰይጣን ጋር፣ 82)

ጌታሲሰቀል በቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ዕድሜልኩን በኃጢኣት ተዘፍቆ ሲኖር በመጨረሻዋ ሰአት ወደልቡ በመመለሱ ሲኦልን ሳያያት አዳምን ቀድሞ ገነትን ከፍቶ ገባ እኛም ካወቅንበት የተሰጠን ጊዜ መመለሻ ነውና እናስተውል ይለናል፡፡

**3.6.3 የእንቢተኝነት ግጥሞች**

ቀጥፎ በልቶ ሞትን እንዳይሞት

ትእዛዝ ሆኖ ሲሠራለት

ከዕፀ በለስ እንዳይበላ

ከአምላኩ ቃል ሲነገረው ብሎት ችላ

ትእዛዝ ሽሮ ያንን በልቶ

አዳምና ሔዋን 5,500 ዘመን ከገነት ተባረው በዚህ ምድር በመከራ ኖረው ሲሞቱ በሲኦል ለመሰቃየት የበቁት የአምላክን ትዕዛዝ በመተላላፋቸው ነው፡፡ ይኸውም “አትብሉ!” የተባሉትን በመብላታቸው ነው፡፡ ከ 5,500 ዘመን በኋላም እነርሱን ለማዳን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተስቅሎ ‹‹የዘለዓለም ሕይወት እንድታገኙ ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ›› ብሎ ሰጠን፡፡ (ሉቃስ ም 22÷19-20) ነገር ግን

ካሣ ሆኖ በመስቀል ላይ ተሰውቶ

ብላ ሲለው ፍቅሩን ሰጥቶ

የአምላክን ቃል እንደቀድሞው አለማክበር

ሁሌም ዐመፅ እንቢ ማለት

የሰው ነገር፡፡ (ከሰይጣን ጋር፣ 11)

ያኔ እንዳትሞት አትብላ ሲባል “እምቢኝ!” ብሎ በልቶ ሞተ፡፡ አሁን ደግሞ የሞት ሞትን እንዳትሞቱ “እንካችሁ ብሉኝ!” ቢል እነሆ አመሉ አልለቅህ ብሎት ዛሬም የሰው ልጅ በእንቢታው እንደጸና የመሆኑን ነገር በትዝብት ያካፍላል፡፡ ይወቅሳልም፡፡

ሸክላዬ

ውበት ቁመናዬ

ገጣሚዋ የሰውን ገላ በሸክላ መስላ አቅርባልናለች፡፡ ሸክላ በአፈር እንደሚሰራ ሁሉ ሰውም ከአፈር ተፈጥሯል፡፡ በሸክላ የተሰራ ዕቃ እንደሚያምር የሰውም ልጅ ውብ ሆኖ ተፈጥሮአልና ነው፡፡

መውደቁን አላየ

አቡክቶ ከሠራው

ከአምላኩ ተለየ

ሸክላ ከወደቀ እንደማይነሳ ሁሉ የሰው ልጅም እንዲሁ ነው ሰው ከአምላኩ ከተለየ ወዳቂ ተሰባሪ ነው፡፡

መሰበሩን ዐውቆ

ምነው ባልታበየ (ከሰይጣን ጋር፣ 24)

መታበይ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ ለሰይጣንም አልበጀ ዕመቀ ዕመቃት አውርዶታል፡፡ ሰውም ዛሬ ቢያምር ነገ ሚች በስባሽ ነውና ይህን ተገንዝቦ በትሕትና ቢኖር፣ባይታበይ ካምላኩም ባይለይ ምን ነበረበት? በማለት በሰው ጠባይ ሐዘኗን ትገልፃለች፡፡

# ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና ትኩረት ያደረገው ለይዘት ትንተና ነው፡፡ በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ የሚገኙት ግጥሞች በውስጣቸው በያዙት ሀሳብ መሰረት ለእግዚአብሄር፣ለድንግል ማርያም፣ ለቅዱሳን መላዕክት፣ ለቅዱሳን አባቶች፣ በመፅሀፍ ቅዱስ ተዐምራት ስለተደረገላቸው ሰዎች እና ስለ ልዩልዩ ጉዳዮች የተገጠሙትን በወገን በወገናቸው በመከፋፈል እንዲሁም እያንዳንዱን እንደገና የምስጋና፣ የልመና፣ የንስሀ፣ የስብከት፣ የነፍስና የስጋ ሙግት እና የእንቢተኝነት በማለት ትንተና ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

በአጠቃላይ ግጥሞቹ ሲታዩ የስብከት ግጥሞች ከፍተኛውን ቦታ ይዘው ይገኛሉ ፡፡ይዘቶቹ የእግዚአብሔርን የባህሪ አምላክነት፣ዘላለማዊነት፣ ቸርነት፣ ይቅርባይነት! የድንግል ማርያምን የአምላክ እናትነት፣አማላጅነት፣ሩህሩህነት፣የመላዕክትንና የቅዱሳንን ተራዳኢነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንደሚገልጹ አይተናል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ጥናት ስለ ነፍስናስጋ ሙግትና ስለ ሰው አስቸጋሪ ባህሪ የሚገልፅ! እንዲሁም ግብረገብን የሚያስተምርና የምዕመናን መንፈሳዊ ህይወት እድገት ላይ የሚያተኩር ይዘት ያላቸው ግጥሞች ተሰተውለዋል፡፡

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. “The things or substance in receptacle or enclosed place is called content. This one refers to the topics ideas, statements, or facts in a book. Document latter or other literary selection as its content the term is generally anonymous with subject matter or substances” (Philip J. stone, 1966, P.5)

2. Christian poetry is any poetry that contains Christian teachings. Themes or references. The influence of Christianity or poetry has been great in any area that Christianity has taken hold. Christian poems often directly references the Bible, while others provide allegory.

# ዋቢ መፃሕፍት

መልከፀዴቅ (ሊቀ ጳጳስ) ::ትምህርተ ክርስትና:: አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1984::

መፅሐፈ ቅዳሴ በግዕዝ እና በአማርኛ ከነምልክቱ:: አዲስ አበባ፣አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1993::

ሰለሞን ደሬሳ:: ልጅነት አርባ ተኩል ግጥሞች:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1963::

ስንታየሁ አባተ እና ብርሀኑ አድማሱ:: ስነ-ፍጥረት:: አዲስ አበባ፣ኢትዮ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት፣ 1996::

ብርሀኑ ገበየሁ:: የአማርኛ ስነ-ግጥም:: አዲስ አበባ፣አልፋ አሳታሚዎች፣1999::

ብርሀኑ ጎበና:: ኖኅተ ሀይማኖት:: አዲስ አበባ ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

ተአምረ ማርያም:: አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገ/ስላሴ ማተሚያ ቤት፣1988::

ታደሰ ወርቁ ::አውደ ስብከት:: አዲስ አበባ፣ኤማይ ማተሚያ ቤት፣1988::

ኃይሉ ገ/ዮሐንስ:: በረከተ መርገም:: 1966::

አለማሁ ሞገስ:: የአማርኛ ግጥም እና ቅኔ ማስተማሪያ:: አደስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1954::

አስማረች ተሾመ::‹‹በሐመር መፅሄት ላይ የወጡ ግጥሞች ዝርዝር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር››::አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የአርትስ ባችለር ዲግሪ የጥናት ማሚያ ፅሁፍ፣ 1998::

አስራት ገ/ማርያም:: ትምህርተ መለኮት:: አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣1991::

አያልነህ ሙላቱ:: ማን ይሆን የበላ:: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣1984::

እሸቱ ታደሰ:: የንስሀ ህይወት:: አዲስ አበባ፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1990::

ኦርቶዶክሳዊ ስነ-ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ፣በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ. የሰ/ት/ቤቶች ማደራጃና መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን የመዝሙር እና የስነ-ጥበባት ክፍል፡፡

ከሰይጣን ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅና ሌሎች፡፡ አዲስአበባ፣ሜጋ ማሳታሚያ ኃላ/የተ/የግ/ማ፣1995፡፡

ወርቂቱ ቱፋ፡፡‹‹ የዘማሪ ይልማ ሀይሉ የመዝሙር ግጥሞች የይዘት ትንተና፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የአርትስ ባችለር ዲግሪ የጥናት ማሟያ ፅሁፍ ፣1997፡፡

ወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜው፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1966፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድረጅት፣ 1992፡፡

የውዳሴ ማርያም እና የቅዳሴ ማርያም ንባብ እና ትርጓሜ፡፡ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ የመፅሀፍት ድርጅት፣1983፡፡

ያዕቆብ ሰንደቁ፡፡ እናታችን ፅዮን፡፡ አዲስ አበባ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣1994፡፡

ይልማ ከበደ፡፡ የአማርኛ ስነ-ግጥም፡፡ አዲስ አበባ፣ ያልታተመ ፣1982፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡ ‹‹በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዲፕሎማ መርሀ ግብር የሚሰጡ አቢይ ኮርሶች የይዘት ትንተና፡፡›› ለአ.አ.ዩ. ድህረ ምረቃ ት/ቤት የቀረበ ጥናት፣ 1986፡፡

ገዛኸኝ ጌታቸው፡፡ ‹‹መልክአ መልክ››፡፡ ሐመር፣ ገፅ 12፣ ኀዳር/ታህሳስ 1995፡፡

ፀጋዬ ገ/መድህን፡፡ እሳት ወይ አበባ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1966፡፡

ቬነስያ እና ሌሎች፡፡ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ኃላ/የተ/የግ/ማ፣1994፡፡

Philip .J. Stone and others. The General Inquire. Cambridge massa chusets and London the mis-press., 1966.

# የግጥሞች ስብስብ

## ኩራትና ትዕቢት

‹‹ኩራት ትዕቢት

የሞሉት እናት÷

ሰይፍና ጐራዴ

የመቱት አንገት÷

አይገላገሉም

እንዲህ በቀላሉ÷

ከመሬት ላይ ወድቀው

ሳይንከባለሉ።››

## ባይኖር ኖሮ ተስፋ

ዙሪያው ሲሆን ገደል

ጨለማ ሲወርሰን

ደስታ ካገር ጠፍቶ

ኃዘን ሲጸናብን

ፈገግታ ተረስቶ

ትካዜ ሲተካ

ኑሮም ሲደበዝዝ

ሲመስል የማይፈካ

ነገም ስትሸሽን

ከአድማስ ስትርቀን

ሕይወት እጅግ መርራ

እሬት ስትሆንብን

ባይኖር ኖሮ ተስፋ

የሚያጠፋጥ ኑሮን

ምድር ትሆን ነበር

የሕያው አስከሬን

የሙታንም መንደር።

## ቅበላ

ምድር አዲስ ስትሆን - ለምለም አንንዴ

ተራሮች ኮረብቶች - ሲቀየሩ ባንዴ

ድፍርሱ ሲጠራ - ሕይወት ስትለመልም

ለመጪው ኖሮዋ - ብርሃን በዓለም

ሞልቶ

አዲሱን ሲያበስር - አሮጌን ሸኝቶ

ፍጥረት አዲስ ሲሆን-
ዘመንንሊቀበልተዘጋጅተሀል

ኃጢያት ያበለዘው - ያጠቆረው ልብህ

አሮጌው ሀሳብህ - ጭንጫው ሰውነትህ

በጽድቅ ለምልሞ - በፍቅር አብቧል?

ድፍርሱ ሀሳብህ - በንስሐ ጠርቷል?

አዲስ ሰው ሳትሆን - ጽድቅን ሳታፈራ

አሮጌውን ሳትጥል - አዲስ መዳረቱ

የዘመን ቅበላ - ይቅር ምናባቱ!

## እናትና ልጁን ያዙ

ማቴ 2÷10

በሄሮድሳዊ ትእዛዝ

በንጉሡ የቅጣት ቁጣ

ከአገር የሚያስወጣ ስደት

ክፉ ቀን የሚባል ሲመጣ

ነፍስ ከውስጥ ስትተክዝ

በሞት ሰቀቀን ተውጣ

በመሸሸጊያው ሲፈለግ

የሚገባበት ሲታጣ

በሩ ተዘግቶ ከልፍኙ

ወደ ስደት ስተጓዙ

ለክፉው ቀን መሸሸጊያ

እናተና ልጁን ያዙ፡፡

ጠላት መውጫ አሳጥቶ

በይሉኝታ ሲሸብበን

በኃጢያት ጦር አስፈራርቶ

ወደ ራሱ ሊማርከን

ዝሙት ሐሜት ምቀኝነት

ሠራዊቱን አስከትቶ

አንገታችንን ሊቀላ

በመንገዳችን አድብቶ

አቅም ሲጠፋ ጉልበቱ

ጠላትን መከላከያ

የያዙት ከንቱ ሲሆን

ላንድ ጀንበር መጠለያ

ሥጋ ከሥጋም ላይሻል

በራስ መመካቱ ቀርቶ

ከሞት ማምለጡ ይበጅል

እናትና ልጁን ጠርቶ፡፡

## እኔም በመቅደሱ ልጽና

ሉቃ.13÷10-13

ወርቅነሽ ቱፋ

አሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ

ቤተ መቅደስ ማገልገሉ

ጎብጠሽ

ከሰውነት ተረ ወጥተሽ

ሳትከፊ

በመጉብጥሽ ሳታኮርፊ

ጸጋ ብለሽ

በተመስገን ተቀብለሽ

ዓይንሽ ከሰው ላይ ተነቅሎ

ጌታን አይቶ ጌታን ብሎ

እሱው መጥቶ ሊጎበኝሽ

በቃሽ ብሎ እስኪምርሽ

ቤተ መቅደስ ውስጥ ተገኝሽ

የመንፈስሽን ጥንካሬ

የእምነትሽን ፉካሬ

እስኪ አስረጂን በጥሞና

እኔም በመቅደሱ ልጽና

## በታምርሽ

ለአባታችን ለሕርያቆስ ዕውቀት ሆነሽ

ለእኛ የሚተርፍ ጥበብ ገልፀሽ

ከአዋራጆች እጅ አዳንሽው

በፊታቸው አከበርሽው

ሞገስ ክብር አክሊል ሆንሽው

ዕውቀት ገልፀሽ አራቀቅሽው

(Sic)ጎሣዕ ልብየ አሰኘሽው

እመቤቴ ብሎ ሲልሽ

ረዳሽው በታምርሽ።

## ምን ይታይሀል ?

ወርቅነሽ ቱፋ

በአምላክህ እጅ ተዳሰህ

እውነት የበራልህ

ስትቆም በአምላክህ ፊት

ስትነሣ ለድኅነት

ንገረኝ ምን ይታይሃል

እውን ዓይንህ በርቶልሀል

የጌታ ክብር ግነቱ

የክብሩ ፀዳል ውበቱ

ቀራንዮ ጎልጎታ

የዋለበት ያለም ጌታ

ትሁት ወዳጅ ቸር እረኛ

ነፍሱን የሰጠልን ለኛ

ወይስ አንተነትክን አየህ

የሰጠህ ውበት ጎላብህ

ጉብዝናህ አዋቂነትህ

ሚታይህ ከሆነ ሥጋህ

ካልረሳሽው ራስህን

ካመለከው አንተነትክን

አታይም በቃ እውር ነህ

አለማየት ነው ኃጢአትህ

እንዲይልህ አይንህ በደንብ

በሰሊሆም ውሀ ታጥብ

አንተን ሳይሆን ጌታህን

እየው እስኪ አምላክህን

‹‹ወስብሐት ለእግዚአብሔር››

## ዳግማዊቷ መግደላዊት

ሰሎሞን ወ/መድኅን/አ.አ/

ከቤተ እግዚአብሔር ርቄ

ከዝሙት መንገድ ወድቄ

በዓለም ውስጥ ስማልል

ቆይ ከነገ ዛሬ ስል

ተቀምጬ በሞት አምባ

ተሳፍሬ የኃጢአት ጀልባ

ከሞት አገር ስኮበልል

መልካም እረኛ ቢያገኘኝ

እጁን ዘርግቶ ተቀበለኝ

በእንባዬ ጠበል ተጠበልኩ

በንስሐ ሕይወት ታጠብኩ

ለሥጋ ወደሙ ታደምኩ፡፡

## ዕድሜህ ስንት ነው?

ዘፍ.47÷8 ከወርቅነሽ ቱፋ

ስንት ዓመት ኖረሀል?

ምን አሳልፈሀል

ምንስ ቀርቶብሀል?

እንደያዕቆብ እየው

ዞረህ ወደኋላ

ስትቀርብ ሚርቅህን

የዕድሜህን ጥላ

ስንት ዓመት አለፈህ

ጌታህን ካወቅሽው?

ተመችተሽዋል

ወይስ ቆረቆርሽው?

ኧረ ለማደግህ

ምን ምልክት አለህ

የኃጢአያት ጡጦህን

ጣልከው ትጠባለህ?

ዛሬም እንደ አምናው

ዳዴን አልጨረስክም?

ማደግህ ሊታወቅ

መራመድ አልቻልክም?

አሊያማ ከደፈርክ አደግሁኝ ለማለት

ስንት ዓመት ኖረሀል

ምንስ ሠራህበት

## ማኀሌተ ጽጌ

ሰላማዊት ከስድስት ኪሎ

አባ ጽጌ ድንግል

አያረጅ ወይ አይሞት

ሙት ይቀስቅሳል

በደረቀው ሌሊት

ምን ዓይነት ጥበብ ነው

ላንተ የተገለጸው

ላፍታ እማያቋረጥ

ገነት ጅረት ነው

ፍጥረት ተጎነጭቶ

ጠጥቶ እማይጠግበው

ምድርና ሰማይ

እንድ ሆነው አብረው

በጽጌ ማኀሌት

ታዬ ተጣጥመው

ልቤ ተደስታ

ነፍሴ ስትለመልም

የገባሁ መሰለኝ

ከጽርሐ አርአያም

## ልብ መንታ

ሰላማዊት

ሲቀደስ አስቀዳሽ

ሲዘፈን አቀንቃኝ

በከንቱ የሚሮጥ

ጊዜውን አባካኝ

እዚያም እዚህም ሲል

ካንዱ አይጠቃለል

በእድሜው ይጫወታል

ብልጥ መሳዩ ቂል

በብልጭልጭ ዓለም

ቆሞ ይታለላል

አምላኩ ሲጠራው

መምጣት ይከጅላል

ስደተኛ ሆኖ

ከሁለቱም ሀገር

ሁለት ያጣ ሆኖ

በከንቱ እንዳይቀር

ልበ መንታነቱ

ይወገድ በእምነት

ጽናትን ይታጠቅ

እንደ አበው ቀደምት፡፡

## የሚያየኝ አየሁት

ዘፍ 16÷13-14

ከወርቅነሽ ቱፋ

በበረሀው በዚያ ንዳድ ስቅበዘበዝ

ሰላም አጥታ ነፍሴ ከውስጥ ስትተክዝ

ተጨንቄ መግቢያው ጠፍቶኝ

ሜዳው ገደል ቀኑ ጨለማ ሆነብኝ

ዘመድ ገደል ምስኪን ፍጡር

ተስፋ የለሽ ሆኜ ነበር

ተገፍቼ ተረስቼ ወገን ባጣ

ድምጽ ከሰማያት መጣ፡፡

አጋር አለኝ ስሜን ጠርቶ

የልቅሶዬን ድምጽ ሰምቶ፡፡

ከላይ ሆኖ ቁልቁል እኔን ሲመለከት

ቀና ብዬ እኔም ያየኝን አየሁት

ቸር አባቴ እንዳልረሳኝ ተረዳሁት፡፡

አይዞሽ ቢለኝ ተስፋ በውስጤ ታደሰ

ቃሉን ልኮ ደረቅ ሕይወቴን አራሰ፡፡

## ቤቴልሔም

የሴም በረከቱ

ማዕከለ ምድር

የተገናኙብሽ

ሰማይና ምድር

የዳዊት መንበሩ

የይሁዳ ርስት

መሶበ ወርቅ የሆንሽ

ለሰማዩ ኅብስት

የብርሃን መሰላል

የተዘረጋብሽ

ከነሠራዊቱ

ንጉሥ ያረፈብሽ

ከአርያም ዙፋን

ከአባቱ ሳይለይ

ረቂቅ መለኮት

ሥጋ ለብሶ ሲታይ

ቤተልሔም ሆነች

የእርቅ አደባባይ።

**ገና መጣ ገና ሄደ**

ወርቅነሽ ቱፋ

ቀን ቀንን ፀንሶ

ዓመት ዓመትን ወለደ

መላእክት የዘመሩበት

ጊዜያቱም ነጎደ

የመሲህ መወለድ

የምሥራች ከታወጀ

ስንት ዘመናት አለፉ

ዓመት ዓመታትን ዋጀ

ስንቴ ሰላም ተባባልን

በእንኳን አደረሰህ ሰበብ

ብዙ ስጦታም ጎረፈ

የመልካም ምኞታችን ግብ

ስንት ሺ ሻማዎች በሩ

የሕጻኑን ልደት ለማብሰር

በዓላት አሳለፍን

ስለልደት በመዘመር

ገና-የኛ ልብ ዛሬም ገና ነው

አምላኩን ለማስተናገድ

መሆን አቅቶን ግርግሙን

እንጓዛለን በልማድ

ገና መጣ ሄደ

በዓል ከሆነ ኑሮአችን

የይሁዳን ኮረብታ እረኞች

መቼ ይሆን መምሰላችን

## ሰው የለኝም

አበባው ዘውዱ

‹‹ውኃው የቤተሳይዳው

የሰሊሆም መጠመቂያው

ሕመም ደዌን ማስወገጃው

መቼ ይሆን……. ሚናጠው››

…….እያለ ወደ ውኃው ሁሉም ያያል

አሁን አሁን

አሁን ጊዜ አንዳች የለም

ሁሉም ነገር ፀጥ ብሏል፡፡

*          *             *

‹‹የኔ ሕመም ካንተ ይብሳል

ከባልሽም ባሌ ይበልጣል

ሰው የለኝም ምን ይሻላል?››

ሁሉም ይላል፡፡

*          *             *

‹‹አንተ ውኃ መጠመቂያው››

አንተ መልአክ ፈጥኖ ሰሚው

እባክህን ተነቃነቅ

ሰው የለኝም የኔን የሚያውቅ

ሰው የለኝም ሰው የምለው

ሰው የለኝም የኔ የምለው

ሽባነቴን ፈውስና

‹እኔን› ስጠኝ የኔ ይሁን እንደገና፡፡

## ተነስቷል

ሙሉነሽ

ሥጋ ተዋሕዶ

በፈቃዱ ቢሞት

እንዴት ተዘነጋ

የወልድ ጌትነት

በደረቅ ግንባር ላይ

ዓይንን የፈጠረ

ከሳሹን ዲያብሎስ

በቃል ያሳፈረ

የነቀለዮጳ

የመንገድ ስንቃቸው

የነሙሴ አምላክ

የአልአዛር ትንሣኤ

የሠለስቱ ምዕት

መሪ አፈ ጉባኤ

የተዋሕዶን ምሥጢር

ፍፁም ያልተረዳው

መቃብሩን ከቦ

ታጥቆ ሲጠብቀው

ተነሥቷል ተነሥቷል

የአብ ቃል ሕያው ነው።

## ሁለቴ ተዳሰስ

ወርቅነሽ ቱፋ

አንድ አይበቃህም ተመለስ

ራስን ማወቅ ተስኖሀል

ዛፍን ከሰዎች መለየት

እንዴት ሆኖ ይቻልሃል?

የዕውቀት ዓይንህ ሊበራ

መዳሰስ ልመድ አንዳንዴ

ተቀመጥ ከአባቶችህ ሥር

ብቃት አይገኝም ባንዴ

ድጋሚ ተዳሰስ መጥተህ

ዓይኖችህ አጥርተው ይዩ

ተለማኝን ከለማኙ

ዛፉን ከሰው እንዲለዩ

## የሰውነገር

ቀጥፎ በልቶ ሞትን እንዳይሞት

ትእዛዝ ሆኖ ሲሠራለት

ከዕፀ በለስ እንዳይበላ

በአምላኩ ቃል ሲነገረው ብሎት ችላ

ትዕዛዝ ሽሮ ያንን በልቶ

ካሣ ሆኖ በመስቀል ላይ ተሰውቶ

ብላ ሲላ ሲለው ፍቅሩን ሰጥቶ

አምላክን ቃል እንደቀድሞው አለማክበር

የሰው ነገር።

ስንታየሁ ዓለማሁ

ከአማኑኤል ካቴድራል

## ሽክላዬ

ሽክላዬ

ውበት ቁመናዬ

መውደቁን አላየ

አብኩቶ ከሰራው

ከአምላኩ ተለየ

መሰበሩን ዐውቆ

ምነው ባልታበየ

ከወርቅነሽ ቱፋ

## እንደ እግዚአብሔር ማን ነው?

ያለ ትናንት ቀዳማዊ

ያለ ዛሬ ማዕከላዊ

ያለ ነገ ደኀራዊ

ከዘመናት በፊት የነበረ

ያለ ድካም የፈጠረ

የማይሸሙት ንጉሥ

እሳት የማይዳሰስ

የማያበድሩት ባለጸጋ

ሁሉን የማይዘነጋ

ከኻሊ ኩሉ አልፋና ኦሜጋ

እንደቸርነቱ አባታችን

ማነው እሱ

እንደ እግዚአብሔር አማላካችን?

ሰላማዊት 6 ኪሎ

## ተዘከሩኝ

ጴጥሮስ ወዮሐንስ

ጣሉልኝ ምጽዋት

አምላክ ከሰጣችሁ

ካላችሁ በረከት

የምግባር ድሀ ነኝ

የዕለት ጾም አዳሪ

ጽድቅን እጠግብበት

ስጡኝ ፍርፋሪ

ፍቅርና ደስታ

ሰላምና ትዕግስት

እምነት የዋህነት

ቸርነት በጎነት

ጥቂት ተዘከሩኝ

ባዶዬን ልሙላበት

ከወርቅነሽ ቱፋ

## አልፈርድብሽም

የጌታዬን ሕጉን

ትዕዛዙን ሽሬ

ማንም እንዳያየኝ

ራሴን ሠውሬ

የኃጢያት ድንኳን

ጨለማን ጋርጄ

ባልባሌ ሕይወት

በሱስ ተጠምጄ
አይሁድ ዘመዶቼ
ሳመነዝር ያዙኝ
አላዘኑልኝም
ለፍርድ አቀረቡኝ
በደሌን ሲሰማ
ቸሩ የእኔ ጌታ
በጣም አዘነልኝ
በመቆጣት ፈንታ
‹‹የጠፋሽው ልጄ
ዛሬ አገኘሁሽ
እንዳትበድይ
ለወደፊት ደግመሽ
እኔ አልፈርድብሽም››
ብሎ አሰናበተኝ
አባታዊ ፍቅሩን
በልቤ ሳለብኝ፡፡

ሱናማዊት ከ6 ኪሎ

## ፊደል ሰው ገደለ

‹‹እናትና ልጁ ተጣሉ
ካንቺ ምን አለኝ ስላላት
የምልጃ ነገር አቆመ
ማርያም ከተአምሩ ምን አላት››
ተባለ አስባለ
እነ እያውቁን አስሞኘ
ፊደል ተገልብጦ
በሞት ተሰናኘ
ዳሩ እናትና ልጅ ተግባብተው
ልመናዋ እንዳይቀር ሳይደረግ
በ‹‹የሚላችሁን አደርጉ››
ከውርፊት ዳነ ባለሠርግ
የወይን ጠጁ ተቀድቶ
ጋኑ ሁሉ ሞልቶ
እድምተኛው ሁሉ ረካ
እናትና ልጁ ተግባብተዋል ለካ

ወርቅነሽ ቱፋ

## መክሊት ነው

ዘመን ተለውጦ
በዘምን ሲተካ
ሁልጊዜ ደስታ ነው

ዘወትር ፋሲካ
መደሰት ባልከፋ
ጸጋ ዕድሜ ሲሰጠን
መገኘት ነው እንጂ
ፍሬውን አፍርተን
ዛሬ እንድንነቃ
ተኝተን የነበርን
እንድንሠራበት
ስለሰጠን ዘመን
አዲስ ጉልበታችን
ስንፍና ሳጠቃን
የንስሐ ዕድሜ
በኃጢአት ለወደቀን
ፍሬ ላላፈራን
ወቅቱ ያዝመራ ነው
ጊዜ ሳወቀበት
ማትረፊያ መክሊት ነው፡፡

ሙሉነሽ/አ.አ/

## የበለሷ ምሥጢር

በሩቁ ለሚያየት
ዙሪያዋን ለምልማ፣
ሠፋፊ ልብሶቿን
ቅጠል ተሸክማ፣
በጣም ታንጓለች
በተለይ ለራበው፣
ፍሬዋን ሲበላ
መንገድ ለጀመረው፣
አጠገቧ ደርሶ
በእጁ ቢዳብሳት፣
ከቅጠል በስተቀር
በለሷ ባዶ ናት፣
ያ የተራበ ሰው
እጅግ አዘነላት
እራሴን እያሳየኝ
ጠርቶ በቁም ነገር፣
ደገዳግሞ መከረኝ
የበለሷን ምሥጢር፣

ሙሉነሽ

## ይበዛል

ጠይቁ ካደረክልኝ

ሳልጠይቅህ የሰጠኸኝ

……..ይበዛል

ከተወረወረብኝ ከማየው ጦር

የሰወርከኝ ከማላየው ጾር

……..ይበዛል

ስምህን ሳልጠራ ከዋልኩበት

ከኔ ያልተለየህበት በምሕረት

በይቅርታህ የጠራኸኝ ባባትነት

…….. ይበዛል

ከኔ ብርታት ቸርነት (sic)

ከብዙ በደሌ ይቅርታህ

ከአሸናፊነቴ ድልህ

………. ይበዛል

ይበዛል ……. ይበዛል ….. ይበልጣል

እንዲበዛልኝ መጥተሀል

እንዲበዛልን ሞተሀል።

መታሰቢያ መስፍን አ.አ

## መኖርን ሳትኖር

ትዕዛዙን ሰምተህ

ቃሉን እያወቅኸው

መቼ ታገልክና

ሥጋን አሸነፍከው

ወድቆ መነሳት

ተሰብሮ መጠገን

ማዕበሉ ሲያይል

በጌታህ መታመን

በተስፋ ስትወጣ

የመከራን ዳገት

አክሊሉ ይታይህ

የዘላለም ሕይወት

ዓለማ ሳይኖርህ

በልማድ ተጉዘህ

መኖርን ሳትኖር

ለምን ትሞታልህ

ሱናማዊት

## እርዳኝ ፈጣሪዬ

ድኅውን አንግቤ ጸናጽሉን ይዤ

በምስጋና ጅረት ሰማያት ሰማያት ተጉዤ

በተመስጦ ፈረስ መሻትህን ሳደርስ

ፍቅርህ ለኔ በዝቶ በስብሐት ተክኜ

ባይፈቅድም ብቃቴ

ቢጎድልም እምነቴ

እኔም እንደ አቅሜ አደግድጌ ቆሜ

በሰጠኸኝ ጸጋ ባብቴ ተጠቅሜ

ሳልርቅ ከመድረስህ (sic) በእምነት ተተክዬ

እንዳመሰግንህ እርዳኝ ፈጣሪዬ፡፡

ስንታየሁ ዓለማየሁ

ከአማኑኤል ካቴድራል

## ስንት ጊዜ ይቅር ልበል?

መቴ 18÷21

ልኑር አልኩኝ እንደቃልህ

እንደፍቃድህ ላሳልፍህ

ለበደሉህ መካስህን

ዓለሙ ሲሰቅልህ በግፍ

እኔም አንተኑ ልከተል

እንደሀሳብክ ልመላለስ

ስንት ጊዜ ሁሉን ልተው

የበደሉኝንስ ልካስ

ዐይኔ ሲለይ ከመስቀሉ

ጆሮዬ ሲርቅ ከቃሉ

እላለሁ ስንቴ በደለኝ

በቂም አረንቋ ስወድቅ

የበደልን ካባ ስለብስ

ሰባት ጊዜ ሰባ ይቅርብኝ፡፡

ቃል ከእምነት ያልተዋሐደ

ቀራንዮ ብቻ አሳየኝ

ልቤ ይቅርታን በለመደ፡፡

ወርቅነሽ ቱፋ

## ከዚህ መሐል አውጣኝ

ፍሬ የሌላት ዛፍ

ወይ ያለቀ ሐረግ

መብል ሚሆን ነገር

የሌለው ቢፈለግ

ድንገት ብትጎበኘኝ

ባዶ ቃርሚያ እንዳልሆን

ደግ ሰው የለምና

ከእኛ መካከል ቅን፡፡

ወንድም ለወንድሙ

መረብ ሲዘረጋ

ፈራጅም ሲዋትት

ጉቦውን ፍለጋ

ከቤቴ ሰው ሳጣ

እጅጉን ስሰጋ

ከዚህ መሐል አውጣኝ

አልፋና ኦሜጋ፡፡

ሃሌሉያ ክፍሉ

ከጎንደር

## የነፍስና ሥጋ ቡጢ

ጊዜያችን ካለፈ እንዳይቆጨን ኋላ፣

እንዝፈን አንዝፈን፣ እንጹም እንብላ፣

እንስጥ እንቀማ እየተባባሉ፣

ነፍስና ሥጋዬ በፈቃድ ተጣሉ፡፡

የሚያስታርቃቸው ሽማግሌ ጠፍቶ፣

ደግሞ ላይሰማው ጠባቸው ጎርንቶ፣

በስልሳ ዙር ቡጢ ደግሞም በሰማኒያ፣

እጅግም ቢበዛ መቶ መቶ ሃያ፣

ቆርጠው ሊፋለሙ ተፈላለጉና

ወደሜዳ ገብተው ባንድ ላይ ቆሙና፣

ለየደጋፊያቸው ንግግር ሲያደርጉ፣

ሥጋ ብቻ ነበር የሚታይ በወጉ፣

ከመድረኩ ቆሞ ሲፎክር ሲያገሳ፣

ሲሮጥ ሲንደረደር ሲቀመጥ ሲነሳ፣

ማን እንደሱ ጀግና ማን እንደሱ አንበሳ፡፡

ነፍስ ግን በፍርሃት እንደሌለች ሆና፣

ደጋፊዎቿንም እጅግ አሳዝና፣

ትታይ ነበር ገርጥታ ኮስምና፡፡

ዳኛው ፊሽካ ነፍተው ሲጀመር ያጣጣ፣

ሥጋ ተደርድሮ ሊያቀምሳት ሲቃጣ፣

ነፍስ አሳለፈችው አቅጣጫ ለውጣ፡፡

ሥጋ በደመ ነፍስ ፎክሮ ሲመጣ

ቁጭ ብድግ ብላ ሩጣ ተራውጣ፣

ልትዘል ስትሞክር በስተኋላ ዙሮ

ሰንጎ ያዘና የነፍስን ጉሮሮ፣

ሲያጣድፋት ጊዜ በርግጫ በጡጫ

ሰማይ ተደፋባት ደረሰች ልትወጣ

በስተሃያኛው ዙር አጣች መግቢያ መውጫ፡፡

የነፍስ ደጋፊዎች ሲያዝኑ ሲሳቀቁ፣

ዳኛው ስጋን ገፍተው ነፍስን አስለቀቁ፡፡

ጉረሮ በማነቅ ፋወል በመሥራቱ፣
ሥጋን ተቆጥተው መከሩ ዘበቱ፡፡
መላቅጥ ቢያሳጣት የሥጋ ጨዋታ፣
እንደማያዋጣት መዝና ገምታ፣
በግርግር መሐል ባገኘችው ፋታ፣
ነፍስ ሾልካ ጠፋች ፉክክሩን ትታ፡፡
አሸናፊነቱ ጀግንቱ ታውቆ፣
አስጨንቆ ይዞ ሳያስቀራት አንቆ
ትታው እንደሄደች ሥጋ ይህን አውቆ፣
ያለቅስ ጀመረ ተንዘፍዝፎ ወድቆ፣
ዓይን ጥርሱ ገጦ አረፋውን ደፍቆ፡፡
በኃዘን በለቅሶ ራሱ ፈረሰ፣
አመድ ነሰነሰ በአፈር ተለወሰ፡፡
እንዲያሲደነፋ ሲዘል የነበረ
ከመድረኩ መሐል ሥጋ ወድቆ ቀረ፡፡

ማርዬ ይግዛው

## እኔ ማነኝ?

ከዓለም ቀረጥ ተርታ
ሌዊ ብለህ የጠራኸኝ
ከበለስ በታች ሳለሁኝ
ሳላይህ ቀድመህ ያየኸኝ
ብዙ ያላስተዋልኳቸውን
ያደረክልኝ ውለታ
ድካሜን ወዲያ ጥለህ
ያቆምከኝ እንድበረታ
ስለጥበቃህ ያለሁኝ
ተሰጥቶኝ የመኖር መብቱ
ባለፍኳቸው ጉዳናዎች
የበዛልኝ ቸርነቱ
ከምድር አሸዋም ሆነ
ከሰማይ ከዋክብት ብዛት
ለመቁጠር የማልችለውን
የደግነትህን ብዛት
ራሴን በዚያ ውስጥ ሳየው
ማንነቴን ስመረምር
እኔ ማነኝ ምንም ነኝ
ከቁጥር የማልደመር

ከኤልሻዳይ